
ወርሐዊ መጽሔት | ቅጽ ፬ | መስከረም ፳፻፲፮ ዓ.ም

ጣዕሊት

የአንባብያን አባት

ደራሲና ተርጓሚ ጋሽ ኃይለሥላሴ መሀሪ



"አባቴ ንባብ ከደሙ ጋር የተዋሀደ ነው::"

ጎንደር የኒቨርሲቲ ሳንኮፋ የአንባብያን ማኅበር [ጎንደር/ ኢትዮጵያ]

ማውጫ

03 | ርዕሰ አንቀጽ
04 | ግጥም 1
05 | ቅንጭብጭብ ጭረት
09 | የጭረት ቆይታ
12 | ወግ [ትናንት ወይስ ነገ]
15 | PHOTOGRAPHY
16 | ግጥም 2
18 | እህት ቤተመጻሕፍት
21 | ጥበብና ባሕል
22 | ግጥም 3
24 | Scribbles
25 | ግጥም 4
27 | የመጽሐፍ ዳሰሳ
29 | ግጥም 5
30 | ጥበበኛ እጆች
32 | ደብዳቤ
33 | ግጥም 6
35 | ተናጋሪ ቀለማት
39 | የመንገዳኜት መጣጥፍ
40 | ቅዳሜን ከሳንኮፋ ጋራ
42 | የፌልም ዳሰሳ
43 | ነገረ ጎንደር
44 | ከእስክንድር ጋራ
47 | የግጥም ችቧችን
48 | ግጥም 7

ርዕሰ አንቀጽ

ያልተቀመሰው የመጻሕፍት ዋጋ ነገር

የአንባቢያን መቀነስና የወረቀት መናር ጸሐፍያንን፣ የጋዜጣና መጽሔት አዘጋጅና አሳታሚዎችን ወደ ህትመት ቅነሳና ብዕርን ወደ መስቀል እያስገባቸው ነው። አንዳንዶች ከሚቀር በሚል ሃሳብ የዲጂታል ዓለምን መቀላቀላቸውን ባይካድም እንደቀድሞ መጻሕፍትን እንደ ልብ በኪስ ዋጋ መግዛትና ማሳተም የህልም እንጀራ ሆኗል።

በህትመት ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች እንደሚናገሩት ከሆነ ከኑሮ መወደድና ከምንዛሪ ጭማሪ ጋር ተያይዞ የናረው የወረቀትና ቀለም ዋጋ ሰራተኞቻቸውን እንዲያሰናብቱ፣ ቀድመው ታትመው የወጡ መጽሐፍትን አዲስ ዕትም አለመውጣትና የገቢ ማሽቆልቆል እንደገጠማቸው ይገልፃሉ። እንደ መፍትሔም የአቅራቢዎች መጨመር ከኢኮኖሚ አንፃር የንግድ ፉክክር ስለሚፈጥር ለዋጋ ቅነሳ እንደሚረዳ ያሳስባሉ። ጸሐፊያን በበኩላቸው የተፈጠረው ችግር ከሚያሳትሙት ገጽ እንዲቀንሱና የህዝቡን ፍላጎት ብቻ በማድመጥ ከፈጠራ ስራቸው ተቀርነው እንዲጽፉ መገደዳቸውን ያስቀምጣሉ።

እንደ ሳንኮፋ ይህ የመጻሕፍት ዋጋ ንረት በመጽሐፍት ልገሳ የሚነቀሳቀሰውን ማኅበራችንን እጅግ የሚፈትነው ሆኖ አግኝተነዋል። በዚህ ረገድ እንደ ሀገር የተለያዩ ቤተመጻሕፍትን መገንባታችን መልካም ሆኖ ሳለ የቤተመጻሕፍት ዋና ግብዓት ለሆኑት መጻሕፍትና አንባብያን መንገዱን ካላመቻቸን ገንብቶ እንደማፍረስ የሚቆጠር ስለሚሆንብን ከቤተ መጻሕፍቱ እኩል ለመጻሕፍት ህትመትና አቅርቦት ቢታሰብበት፣ በአንባብያን በኩል ደግሞ ወደ ተለያዩ የማህበራዊ ድህረ ገጽ መርሀግብራት መሳብ ለንባብ ትልቅ ተግደሮት የሞናስቀሞጠው ነው።

ይህን ለመቅረፍ እንደ አንባቢ ለማንበብ መነሳሳት የህትመት ብዛትን ስለሚጨምርና ከብዛት ከሚገኝ ትርፍ አሳታሚዎችን ለማሰራት በማነቃቃት በኢኮኖሚ ስሌት ንረቱን ጋብ ያደርጋል፣ በመንግስት በኩል ለንባብና መጻሕፍት የሚሆኑ ግብዓቶች ላይ የቀረጥ ቅነሳ አሊያም ነጻ ቀረጥ መሆን እንዲሁም በአቅርቦት በኩል ደግሞ በዚህ ዘርፍ የሚሰማሩ ነጋዴዎች መጨመር እና የአቅርቦት አማራጮች መቀመጥ ለጉዳዩ መፍትሔዎች እንደሚሆኑ እናምናለን። ተግዳሮቶቹ እንዳሉ ሆነው ከማንበብ አንጉደል መልዕክታችን ነው።

እናንብብ፣ እንለወጥ፣ እናካፍል

አሳታሚ

ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሳንኮፋ የአንባብያን ማኅበር

ዋና አዘጋጅ እና ኤዲተር

ፍናማርያም

ግራፊክስ ዲዛይን

በ-ግፀዘ የማስታወቂያ እና ኅትመት ሥራ

+251923671919

አማኪኞች

ፍናማርያም

ብሩክታዊት መርሻ

ሩት ኤልያስ

እንዳለ መኮነን

እጸሐይወት ገናናው

ርበቃ

ቀጸላ

ሜሪ ታዬ

ጋብሬላ ታዬ

ፌራኤል ታዬ

ነጃት ሀሰን

ክንዱ ፈጠነ

በኀይሉ ዘለዋሽ መልካሳ

© Copyright
2016 ዓ.ም


እንዳ ቢሉቢሮ ኣበባ ለኣበባ ዐዳይ
እንቡር እንቡር....
በፍቅር ለመክረም !
ዳስ ይሳኬ መስከረም !
[ሙሉጌታ ተስፉዮ]

ቅንጭብጭብ ጭረት

እጅግ የሆነው ዓድዋ በእጅግአየሁ ብዕር [በኀይሉ ዘአዋሽ መልካሳ]



ሙዚቃ ስሜት ነው፤ ስሜቱ እንዲሁ ሊረዳት እንኳ እስኪያስቸግር ድረስ እውስጥ ድረስ ዘልቆ ገብቶ ትካዜን፣ ሐሴትን፣ ፌሽታን፣ ዋይታን...ሌላም ሌላም ነገር የሚፈጥር ድንቅ ስጦታ... ታዲያ ይህን ስሜት በስመ ሙዚቃ ብቻ የትኛውም ሙዚቃ አይፈጥርም። ሙዚቃውን ከሚጫወተው አካል አንስቶ በዘያ ሙዚቃ ሥራ ላይ እስከተሳተፉት የእያንዳንዱ ሰው ጥንቃቄ ሙዚቃው እልብ ውስጥ እንዲቀር ያደርጋል። ሙዚቃ ሁሉ ይህን ስሜት መፍጠር ቢችል ደግ ነበር፤ ግና በዘህን ያህል ከፍታ ለመሥራት መቀባት ያስፈልጋል፤ ከተቀቡቱ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ሙዚቀኞች እጅግአየሁ (ጂጂ) ቀዳሚ ተርታ የምትሰለፍ ናት።

ጂጂ ገና በማለዳው የሙዚቃ አማናዊ ብርሃን በልቧ የበራ የዘመናችን ድንቅ ዘፋኝ ናት፤ ጂጂ በእያንዳንዱ ሥራዎቿ ጠርታት የማትጠግባት ኢትዮጵያ የምትባል የሀገር ረሃብ የልቧን ሆድ በልቶ ያስራባት ሁሌም በጥዑም ልሳኗ ሳትጠራት የማታልፍ እንስት ናት። ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ጂጂ ውስጥ ልዩ ቅላጼ፣ ልዩ ድባብ አላት፤ አስተርዕየቷ ጂጂ ላይ እጅግ ይበዛል። አንድ የትምህርት ቤት ወዳጇ ስለጂጂ ዘፈን ሲያወራ ‹‹የጂጂ ዘፈን ፋርማሲ ተቀምጦ በሐኪም መታዘዝ አለበት›› ብሎኛል፤ እውነቱን ነው የጂጂ ዘፈን ኢትዮጵያዊነት ለሚያሳምማቸው ፈውስን መስጠት ከሚችሉ ጥቂት ዘፈኖች ተርታ ቢሰለፍ የቀዳሚነቱን ቦታ የሚይዙ ናቸው።

ጂጂን ማድመጥ ከጀመርኩኝ የእድሜዬ 3/4ኛ ዘመን ይሆናል፤ በልጅነቴ ምንም በማላውቅበት ሁኔታ ውስጥም ሆነ ዛሬ በጥቂቱ ስለኢትዮጵያ ማንነት ባወቅሁበትም ዘመን የጂጂ ዘፈን እንደ ወይን እየፈላ ጣዕሙን መግለጥ እስኪቸግረኝ ደርሻለሁ። በተለይ በዘህ ወቅት በየቀኑ ፈዋሽ ሥራዋን ሰማለሁ።

በ1993 ዓ.ም ባወጣችውና ‹‹ጉድ ፈላ ዘንድሮ›› በተሰኘው አልበሟ የዛሬ ርዕሰ ጉዳያችን የሆነውን ዓድዋን በማይተካ ብዕር፣ በማይተካ የድምጽ ቅላጼ ከፍ አድርጋዋለች። በኔ ልብ ውስጥ ከዘህ በፊት ከዘህም በኋላ ማንም ስለ ዓድዋ ቢዘፍን የጂጂን ያህል እጅግ የሚያየ የለም እላለሁ (ገዜ ከሰጠን እናየው የለ፧)

ጂጂ ሁሌም ማለት በሚቻል መልኩ የዘፈኖቿ መጀመሪያ ቃላት በኀይል የከፍታ ማማ ላይ ይረግጣሉ ይህም በዘህ ዘፈኗ ታይቷል እንዲህ ስትል፦

‹‹የሰው ልጅ ክቡር፣
ሰው መሆን ክቡር፣
ሰው ሞቷል ሰው ሊያድን ሰውን ሲያከብር፣
በደግነት በፍቅር በክብር ተጠርቶ በክብር ይሄዳል፣
ሰው ሊኖር ሰው ሞቶ።››

የጂጂ ዘፈን ፋርማሲ ተቀምጦ በሐኪም መታዘዝ አለበት›› ብሎኛል፤ እውነቱን ነው የጂጂ ዘፈን ኢትዮጵያዊነት ለሚያሳምማቸው ፈውስን መስጠት ከሚችሉ ጥቂት ዘፈኖች ተርታ ቢሰለፍ የቀዳሚነቱን ቦታ የሚይዙ ናቸው።

ይህ ከፍታ፤ ሰው (ሰብእ) የሚለውን ቃል ማንም ባዕድ ተራ እቃ ሸቀጥ አድርጎ ለማጋዝ ሲያስብ ልኩን ያየበት፤ በሰውነት ማዕረግ ሁሉም እኩል እንጂ ማንም ከማንም የተለየ ተፈጥሮ እንደሌለው በአደባባይ የታየበት ነው። ኢትዮጵያዊነት ማለት ለሰው ሁሉ ዘር የሚያስብ ገፍተው ከመጡበት ስለራሱ ብቻ ሳይሆን ስለሌላውም መጠቃት ሲል እምቢኝ የሚል መሆኑን ዓለም እንዲያውቅ የሚያደርግ መሆኑን ያስመሰከሩበት ነው።

ሰው መሆን ክብር መሆኑን ይህንን ክብርንም ለማሳየት መሞትን እስከመምረጥ የሚያደርስ መሆኑ የታየበት ነው ዓድዋ።
የኢትዮጵያዊነት ሰበዝ ተጠናክሮና ተሰብስቦ ኢትዮጵያ የምትባል ሰፌድ የተሰፋችባት ቦታ ናት ዓድዋ። ዓለም ማንም የበላይ የለም ማንም የበታች የለም ሁሉም የሰው ልጅ እኩል ነው ብሎ ያመነባት መካን ናት ዓድዋ።
ለትውልድ፣ ለሀገር ዳር ድንበር መነካት ዘብ ለመቆም ውጣ ሲባል ለነፍሱ፣ ለስንቁ ሳይሳሳ አበል ሳያስጨንቀው ቀፎው እንደተነካበት ንብ ተምሞ ወጥቶ ድል የነሳባት አፈር ናት ዓድዋ።
ከዚህ ከፍታ ወደሚልቅ ሌላ ከፍታ እንዲህ ትወስደናለች፦

‹‹የተሰጠኝ ሕይወት ዛሬ በነጻነት፣
ሰው ተከፍሎበታል ከደምና አጥንት››

ብዙ ጊዜ ሳናውቀው እንዲሁ የጣልነው፣ ናቅ ያደረግነውን ርዕሰ ጉዳይ ሁሌ እናስተውለው ዘንድ የቆምንበት፣ እየኖርንበት ያለው ሕይወት፣ የተቀበልነው መዳን ምንጩ ሰው የተከፈለበት፣ ደም የፈሰሰበት፣ አጥንት የተከሰከሰበት መሆኑን ታስታውሰናለች። ለዛሬ መኖራችን የትናንቱ መሞታቸው መሆኑን ታስታውሰናለች። የዛሬ መቆማችን የትናንት መዋደቃቸው መሆኑን፣ ዛሬያቸውን መስዋዕት አድርገው ነጋቸውን እኛ ውስጥ ማኖራቸውን እንዳንዘነጋው ታዋየናለች። መስዋዕትነት በቃል ያይደል በተግባር መሆኑን በመድረኩ ላይ የደመና የአጥንት አትሮንስ ዘርግታ ዓድዋ የተሰኘ ስንክሳርና ገድል ታነበንብልናለች።
ከዚህ በኋላ የሰውነትን ክብር ነግራንም የለ? ለምስክርነት ባለቤቷን ዓድዋ ደግሞም እናቷን ኢትዮጵያን ትጣራለች፦
ከዚህ ከፍታ ወደሚልቅ ሌላ ከፍታ እንዲህ ትወስደናለች፦

‹‹ስንት ወገን ወደቀ በነጻነት ምድር፣
ትናገር ዓድዋ ትናገር ትመስክር፣
ትናገር ዓድዋ ትናገር ሀገሬ፣
እንዴት እንደቆምሁኝ ከፌታችሁ ዛሬ››

‹‹ስንት ወገን ወደቀ›› የሚለው ላይ ረገጥ አድርገን ከቆምን ወገንን በሁለቱም ዘውግ እንድናዬ ታደርገናለች። የጠላት ወገንና የድሉ ባለቤት፣ የአቸናፈውን አካል። የርሷ ትርክት ግን የሚደፋው በሀገሬው (በተበዳዩ) ወገን ያለውን፤ እስከነነጡት ድረስ ዝምታ የመረጠውን...እንደፍልፈል ጉድጓድ እስከምስ የታገሰውን...ዓድዋም ሀገራም እንድትናገርላት የፈለገችው ይህንን ወገንን ነው። መናገሯ የሚጠቅመው፣ ምስክርነት መስጠቷ የሚጠቅመው ከፌታችሁ እንዴት እንደቆመች ከእርሷ በቀር ሌላ መስካሪ ስለሌለ ነው። ‹‹ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ›› አይደል ብሒሉ? ታዲያ ለመናገርም ለማርዳትም ድሉን ለመናገር ሞቱንም ለማርዳት ከዓድዋ በላይ ማን አለ? ተራራውን ሰናየው በራሱ ውስጣችን ውስጥ ይህንን ምስክርነት ሁሌም ዓድዋ የምትመሰክር እስክትመሰለን ድረስ ዓድዋ አሰውባ አሸሞንሙና አቅርባታለች።
አትሮንሱ ላይ ያለውን ስንክሳር ከእንዲ ገጽ ወደሌላው ገጽ ስትገልጥ በፌታችን መቆሟን በመነቀጥቀጥ እና በፍቅር ድፍረት እንደህ እያለች ነው፦

‹‹በኩራት በክብር በደስታ በፍቅር፣
በድል እኖራለሁ ይኸው በቀን በቀን በቀን በቀን፣
ደግሞ መከራውን ያን ሁሉ ሰቀቀን››

ነጻነቷ ያስገረማት፣ ያስደነቃት፣ ከአቅሟም በላይ ልትከፍለው ያልቻለችው ደግሞም በሞን እንደሞትከፍለው የቸገራትም ትመስላለች ለዚህም ነው ስንኙን ስትቋጨው ‹‹ደግሞ መከራውን ያን ሁሉ ሰቀቀን›› ያለችን።
በሰዓታት ውጊያ የተገበረው ሕይወት ነውና ለዛሬ መቆሟ እሞቢኝ ማለታቸው ነውና ዛሬን ይህን የነጻነት አየር ያስተነፈሰን። የሀገር ልጅ በአንድ ከትሞ በአንድ መሸን በድብቅ ያይደለ በግልጥ፣ የፈሪ ግጥሞያ ያይደለ የጀግና ግጥሞያ ደረቱን እና ግንባሩን ሰጥቶ ሞትን ድል የነሳ፤ የአጥብያው ኮከብ ዓላማው ላይ የሰቀለ ነው። ይህ ሁሉ ተደማምረውባት በድል መኖሯ በቀን በቀን መሆኑን የሞታውጀው አባቶቿ አላዋረዷትምና በሞትኖርበት ቦታ ከሌላው በተለየ ጅጋኔን ተመልታለችና ስታዜመው ከእርሷ ላይ ነጻነቷ በዜማ እኛ ውስጥ ይጋባል ውስጣችን በእያንዳንዱ ስንኝ የመወረር ስሜት ይሰማናል።
የግጥሟን ከፍታ ከዚህ በኋላ በብረሃን ዓመት ታሰላብናለች ድምድማቷ ይናፍቀናል ባላለቀ እንላለን እርሷም ከፍታዋን ልታሰገርመን፦

‹‹ዓድዋ ዛሬ ናት ዓዋ ትናት፣
መቼ ተረሱና የወዳደቁት››

ብላን የኛን በሚገባቸው ልክ አለማክበር እያወሳች ታስቆጨናለች፤ አሁንም አታርፍዱ ገዜ አለን ‹‹ዓድዋ ዛሬ ናት›› ትለናለች። አንዷን ዓድዋ በገዜ ሰሌዳ ሠስቱንም ክዋኔ ትሰጣታለች፤ የበኸር ስሟን ትናንት፣ ደግሞ ዛሬም ትላታለች። ሁሌ ዘፈኑን ሰናደምጠው ዓድዋ ዛሬም መሆኑን እንዳንዘነጋ ታስታውሰናለች። ለዚህ ምክንያት ስትጠራም የወዳደቁት መቼ ተነሱ ትለናለች። ለካ ይህም እዳ አለብን። የረሳናቸው ስማቸውን ብቻ ሳይሆን ውለታቸውን የረሳናቸው ብዙ መሆኑን ታስታውሰናለች፤ ታሳስበናለችም።
ይህንን አሳስባን ከስሳን ብቻ አታቆምም አማናዊት መምህርት ናትና እኛ የገጠመን ዝንጋኤ አልገጠማትምና እንደ ንስር ከዝናማት በላይ በግጥም ክንፎቿ ትበርና ቀልቀል እያየችን እኛ የረሳነውን የዘወትር ሥራዋን ይህን የምስጋና መስዋዕት ከመስዋዕት ማቀጠያው ቦታ ሆና ዐይኖቿን አንስታ እንዲህ ትቀኛለች፤ ስባሔዋንም ታደርሳለች፤ በነግህ፣ በቀትር፣ በሰርክ አታስታጉልም፦

‹‹ምስጋና ለእነርሱ ለዓድዋ ጀግኖች፣
ለዛሬ ነጻነት ላበቁኝ ወገኖች።።››





ብላን የኖን በሚገባቸው ልክ አለማክበር እያወሳች ታሰቆጨናለች፤ አሁንም አታርፍዱ ገዜ አለን ‹‹ዓድዋ ዛሬ ናት›› ትለናለች። አንዷን ዓድዋ በገዜ ሰሌዳ ሦስቱንም ክዋኔ ትሰጣታለች፤ የበኸር ስሚን ትናንት፣ ደግሞ ዛሬም ትላታለች። ሁሌ ዘፈኑን ስናደምጠው ዓድዋ ዛሬም መሆኑን እንዳንዘነጋ ታስታውሰናለች። ለዚህ ምክንያት ስትጠራም የወዳደቁት መቼ ተነሱ ትለናለች። ለካ ይህም እዳ አለብን። የረሳናቸው ስማቸውን ብቻ ሳይሆን ውለታቸውን የረሳናቸው ብዙ መሆኑን ታስታውሰናለች፤ ታሳስበናለችም።

ይህንን አሳስባን ከስሳን ብቻ አታቆምም አማናዊት መምህርት ናትና እኛ የገጠመን ዘንጋኤ አልገጠማትምና እንደ ንስር ከዝናማት በላይ በግጥም ክንፎቿ ትበርና ቁልቁል እያየችን እኛ የረሳነውን የዘወትር ሥራዋን ይህን የምስጋና መስዋዕት ከመስዋዕት ማቃጠያው ቦታ ሆና ዐይኖቿን አንስታ እንዲህ ትቀኛለች፤ ስባሔዋንም ታደርሳለች፤ በነግህ፣ በቀትር፣ በሰርክ አታስታጉልም፡-

‹‹ምስጋና ለእነርሱ ለዓድዋ ጀግኖች፣
ለዛሬ ነጻነት ላበቁኝ ወገኖች።።››

ይህን ሁሉ መዓት ችላ የምታነባዋ እምዬ ኢትዮጵያ በልጇ በጂጂ ዘወትር ትደሰታለች ደግሞም ትመሰገናለች። የልጆቿን ውለታ አልረሳችምና ምስጋና ማድረሷን አልተወችምና፡ ፡ ጂጂን ዘወትር ታሞካሻታለች። ኢትዮጵያ በጂጂ ደስታዋ ወደር የላትም።

እምባ አባሿናትና ጂጂዬን ጂጂዬን ልጇን ትላለች...እርሷም በእናቷ ፍቅር ሁሌም ትቃትታለች። ሁሌም በመገናኛው ድንኳን ስትቆም በዛ ተሰረቅራቂ ድምጿ እናቷን ከአንጀቷ ውስጥ ትፈልጋታለች። ደግሞም ታገኛታለች። አግኝታትም ፍቅሯ ይከብዳትና የማይታበስ የሚመስል እምባዋን ታዘንበዋለች።

እናቷም በሕቡዕ መዳፏ እምባዋን ስታብስላት እርሷ ብቻ ታያለች በዚህም ተገርማ ከታዛው በደስታ ለመውረድ ከወጣችበት ከፍታ ከፍ ብላ ላያት ሁሉ ርቃ ድምጿን ብቻ እንዲህ ከግጥሚ ከሚወጣው የጨረር ፍንጣቂ የተነሳ ርሷን ማየት ይከብዳልና ፌትሽን ተሸፈኝልን ልንላት እንዳዳለን። ርሷ ለዚህ ውዳሴ ከንቱ ቁብም ሳትሰጥ፡-

‹‹የጥቁር ድል አምባ ዓድዋ፣
አፍሪካ እምዬ ኢትዮጵያ፣
ተናገሪ ተናገሪ
የድል ታሪክሽን አውሪ›› ብላ ከደርቡ ትወርዳልች።

ይህች ቅኔ የሆነች ቅኔያዊት እጅግ የሞታይ እንስት እጅግ የሆነውን ዓድዋ ዘወትር ለመስማት እንዳይከብደን አድርጋ እልባችን ጽላት ላይ ዓድዋን ቀረጸችብን። ይህንን ጽላት አውጥተው የሸጡትም፣ የሰበሩትም ላይ ደግማ ደጋግማ ትቀርጽባቸዋለች እርሷ እቴ አይደክማትም።

ታዲያ በዚህች እንስት ሥራ በፍቅር የማትወድቅ፣ የኔ ልጅ፣ ብትሆን ብላ የማትመኝ የኔ ልጅ ብትሆን ብላ የማትመኝ ሀገር ትጠፋ ይሆን? ርሷ ግን ለእንዷም ለመጨረሻም የኢትዮጵያ ፍቅር ብቻ እልባ ውስጥ ገብቷል። ላትፋታት አግብታታለች፤ እንደ ርግብ ላትወላውል ቆርባላታለች።

ያልተዘመረልሽ ዘማሪት ሆይ መልክዓ ውዳሴዋን ዘወትር የምትደግሚላት ሀገርሽ ዘወትር ታስብሽ፤ ጂጂዬ ትናፍቂናለሽ ዳግመኛ በሥራዎችሽ ልናይሽ እንወድዳለንና በርቺልን ከሥራዎችሽ ሥር ልንካድም እንወድዳለን!!!››

**እጅግ የሞታይ እጅግአየሁ፣
የተባው ብዕርሽ የተገራው ድምጸፅሽ
ይባረክ!!!!!!**

ዖጢ ቀይ

ጋሽ ኀይለሥላሴ መሀሪ አባት፣ መምህር፣ ተርጓሚ፣ የንባብ ሰውና በንባብም ትውልድ የሚያንጹ የነበሩ ሲሆን ስለ እርሳቸው የህይወት ጉዞ እና ከዕረፍታቸው ኋላ የእርሳቸውን ወደ 1000 የሚጠጉ የመጽሀፍት ስብስብ የሳንኮፋ ቤት እንዴት እንደደረሱ ከሁለት ሴት ልጆቻቸው ወ/ሮ ተዘሩ ኀይለሥላሴና ዶ/ር አደዳ ኀይለሥላሴ ጋር ጭረት እንዲህ ተጨዋውታለች። ሁለቱም ለነበራቸው ፍቃደኝነት ሳንኮፋ ከልብ ምስጋናውን ያቀርባል

ጭረት: ስለ ጋሽ ኀይለሥላሴ ውልደትና እድገት ትንሽ ነገር ብትይን

ወ/ሮ ተዘሩ: አባቴ የተወለደው በቀድሞ የትግራይ ክፍለሀገር ልዩ ስሙ ዋጅራት የሚባል ቦታ ሲሆን አባታቸው አቶ መሀሪ ሸጊ ሲባሉ እናታቸው ወ/ሮ አማረች መርሻ ይባሉ ነበር። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በደሴ ከተማ ወ/ሮ ስኂን ት/ቤት ፡ ሁለተኛ ደረጃን ደግሞ አዲስ አበባ በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ተምሯል። ከዛም ቀጥታ ወደ ማስተማሩ ነው የገባው

ጭረት: መልካም፣ የመምህርነት ጉዟቸውስ እንዴት ነበር?

ወ/ሮ ተዘሩ: ከምኒልክ እንደጨረሰ ወደ አዲስ ዘመን ተመድቦ ማስተማር ጀመረ ትንሽ ቆይቶ የሱፐርቪዥን ስልጠና ወሰደና ወደ ደ/ታቦር በሱፐርቫይዘርነት ማገልገል ቀጠለ፣ ከደ/ታቦር ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ 6 ኪሎ የኒቨርሲቲ በመግባት በ School administration ተምሮ ተመረቀና ጎጃም ክፍለሀገር ፍኖተ ሰላም እየተቋቋመ ለነበረ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር በመሆን ተመደበ፣ በዚያም ሲያገለግል አብዮቱ ሲገባ ለመምህርነት አመለከተ እና ወደ ደብረማርቆስ በአማርኛ መምህርነት ተዛወረ እርግጥ ፍኖተ ሰላምም እያለ አንድ ክፍል ይዞ እንግሊዝኛ ያስተምር ነበር። ትንሽ ቆይቶ ጎጃም ክፍለሀገር ት/ቤቶች ጽ/ቤት ውስጥ የትምህርት አመራር ሥራአስኪያጅ በመሆን ማገልገል ጀመረ ከዛም ተነስቶ በተመሳሳይ መደብ ጅማ ክፍለሀገር ከፋ ውስጥ መስራት ቀጠለ በመጨረሻም አዲስአበባ በመምጣት የትምህርት ክፍል ሥራ ሂደት ውስጥ በመስራት አጠናቆ ጡረታ ወጣ እና ይሄን ይመስላል የስራ ሁኔታው።

ጭረት: ንባብና ጋሽ ኀይለሥላሴ እንዴት ነበሩ፣ እንዴት ታስታውሳላችሁ?

ወ/ሮ ተዘሩ: አባቴ ንባብ ከደሙ ጋር የተዋሃደ ነው። ከቤት ሁሌም ሲወጣ ሁለት መጽሐፍት በኪሱ ይዞ ነው፣ አንደኛው እንብቦ ሲታክተው ሌላውን ደግሞ ይቀጥላል የሚገርመኝ ዓይነት ነገር ነው፣ በአውቶብስ ሲጓዝ ራሱ የአውቶብስ ትኬቶቹን ሰብስቦ ይመታ እና የሚያየውን ነገር፣ ያሰበውን ይጽፍ ነበር። በአንድ ወቅት እንደውም ስለ እጽዋት ማንበብ ጀመረና ጫካ እየሄደ ዛፎችንና የእጽዋት ጥናት ሁሉ ጀምሮ ነበር ጥቅማቸውን ስማቸውን ወዘተርፈ፣ ከንባብ ባለፈ የተጻጻፈውን ደብዳቤ ሁሉ በኮፒ ያስቀምጣል አሁንም በ1940 የተጻፉት እኔ ጋር አሉ።



ጭረት: እንደ መምህርስ ለተማሪዎቻቸው ንባብን እንዴት ያለማምዱ ነበር?

ወ/ሮ ተዘሩ: ለተማሪዎቹ እንደየደረጃቸው መጽሐፍ ይሰጣል፣ ካነበቡ በኋላ የጋራ ውይይት እንዲያደርጉ ያነሳሳቸው ነበር ፣ ከውይይቱም አልፎ ያነበቡትን መጽሐፍ ሃሳብ ለእርሱ እነዲነግሩት ያደርግ ነበር። የሚገርመኝ ተማሪዎቹ ላይ ብቻ ሳይሆን እኛ ልጆቹን ሽርሽር ከወሰደን በኋላ ያየነውን እንድንጽፍና እንድናነብ ያደርገን ነበር። ለእያንዳዳችን ዕለታዊ የግል ማስታወሻ ሰጥቶን የዕለት ውሏችንን ማታማታ እናታችን ቡና እያፈላች እንደ ቤተሰብ የሁላችንም ይነበባል ከዛም ቴፕ ሪከርደር ነበረችው በእርሱ እየቀዳ ያስቀምጠው ነበር። ሌላ የማስታውሰው ማታ ማታ መጽሐፍ ቅዱስ በእንግሊዝኛና በአማርኛ ነበረን እርሱን ሁላችንም እየተቀያየርን እናነብ ነበር። እርሱ ደግሞ ፈረንሰኛውን ይዞ እየተከተለ ያደምጠናል ። አንቺ ለምሳሌ እኛ ቤት ብትመጪ ከሰላምታው በኋላይህንመጽሐፍአንብበሽዋል ብሎ ይጠይቃል ካላነበብሺው እንድታነቢው ይጋብዛል፣ ካለው ደግሞ አውጥቶ ይሰጥሻል ሁሉ ነገሩ መጽሐፍና ንባብ ነበር።

ጭረት: ንባብ ላይ ያላቸው እምነትና አቋም ምን ነበረ?

ዶ/ር አደዱ: ገንዘብን ከመሰብሰብ ይልቅ በማንበብ ትውልድ መስራት ይቻላል ይል ነበር፣ ምንም ነገር በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ አደጋ ልናጣ እንችላለን ሆኖም በማንበብ ያገኘናቸውን ልምዶችና እውቀቶች ማንም አይወስደውም። ማንበብ ስብዕናን ይገነባል፣ ሥነ ልቦናን ያጠነክራል፣የአቋም ሰው እንድንሆንና ሰዎችን እንድንረዳና እንድንረዳ ያግዛል ይላል።

ጭረት: የነበሩት መጽሐፍት ምን ዓይነት ነበሩ? እንዴትስ ያስነብቡ ነበር?

ዶ/ር አደዱ: ቤት ውስጥ ያልነበሩ የመጽሐፍት ዓይነቶች አልነበሩም፣ ከህጻናት ጀምሮ እስከ አዋቂዎች። በትምህርት ደረጃም መደበኛ ትምህርት ለተማሩና ላልተማሩ፣ የህይወት ልምድ ያላቸውና የሌላቸው ብሎ ልክ እንደ graded reading approach አስተካክሎና ከፋፍሎ ያውሳል፣ ያሰነብባልም። እና የሆነ ሰው መጽሐፍ እፈልጋለሁ ብቻ ሰላለ አይጠውም ያ ሰው ምን ማንበብ ይችላል? አቅሙ ምን ይፈቅዳል የሚለውን መዘኖ ነበር የሚሰጠው እናም መጽሐፉቱም ልክ እንደ ቤተመጽሐፍት በካታሎግ(catalog) የተቀመጡ ነበሩ።

ጭረት: የሚያስነብቡት የት ነበር? ቤት ውስጥ ወይስ ይዘው ሄደው ነው?

ዶ/ር አደዱ: እንደ ሁኔታው ነው፣ እዛው ሆኜ አነባለሁ የሚል ካለ እንዲሁም የማንበብ ልምዱ ያልዳበረ፣ በውጪ ሀገር ቋንቋ የተጻፈን ለመረዳት የሚቸገሩ ካሉም እዘያው እሱ እያገዛቸው እንዲያነቡ ያደርግ ነበር። ከሚያነቡት መጽሐፍ ላይ ያልተረዱት ቃልን በወረቀት እንዲጽፉት የቤት ስራ ይሰጥና የጻፉትን ተቀብሎ ከመዝገበ ቃላት አውደዊ ፍቺ ከአንድ አንድ ዓረፍተ ነገር ጋር ለሚያነቡት ልጆች መልሶ ይሰጣል፣ የተቀረት ቤታቸው ወስደው አንብበው የሚመልሱ አሉ፣ ስለዚህ ሁለቱም ዓይነቶች ነበሩ።

ጭረት: መጽሐፍ እንዲያነብ ከሳቸው የተዋሰ ሰው ጋር አንብቦ ሲጨርስ ስለ መጽሐፉ ይወያዩ ነበር?

ዶ/ር አደዱ: በደንብ! ምን አገኘህበት ፣ ምን ተማርክበት ያላል። ለምሳሌ አንድ ሰው መጽሐፍ ጨረስኩ ብሎ ዝም ብሎ መመለስ አይችልም እስቲ ያነበብከውን በአንድ ዓረፍተ ነገር ንገረኝ ነው የእርሱ የመጀመሪያ ጥያቄ፣ አሁን እኔ Gone in the windን አንብቤዋለሁ ብለው ስለምንድነው ብሎ ይጠይቀኛል፣ እኔም እንደዚህ ሆኖ እንደዚያ ሆኖ ስል አይ ታሪኩን ስለምን እንደሆነ በአንድ ዓረፍተ ነገር ንገረኝ እንደዛ ከሆነ መረዳትሽን አውቀዋለሁ ይልና ከነገርከት ይሞግታል፣ይጠይቃል።

ጭረት: ምን ዓይነት መጽሀፍትን ማንበብ ይወዱ ነበር?

ዶ/ር አደዱ: እስከማውቀው ድረስ ወደ ፍልስፍናና መንፈሳዊ ነገሮች ላይ ያተኩር ነበር፣ ዕይታዎችን(imagination) ወደ ሚያሰፋ፣ የቤተሰብ ታሪኮች፣ የአመራርና የቋንቋ ሳይንስ(linguistic) መጽሐፍትም ይመስጠው ነበር።

ጭረት: የጋሽ ኃይለሥላሴ ለተደራሲያን የደረሱና በዘግጅት ላይ ያሉ መጽሐፍት ምን ምን ነበሩ?

ዶ/ር አደዱ: ለህትመት የበቃው ሳቤላ ነው፣ እስካሁንም በመታተም ላይ ያለና በዩንቨርስቲዎች ስለ ሥነ ትርጉም ትምህርት የሚሰጥበት ነው፣ በትምህርት መርጃነት የታተመ ደግሞ "የፍቅር ትንግርት" የሚልም መጽሐፍ አለው፣ እንዳልሽው ደግሞ በዝግጅት ላይ ያሉ፣ ዝግጅታቸውን የተጠናቀቀላቸው ስራዎችም ነበሩት።

ጭረት: ከማንበብና ማስነበብ ባሻገር የነበራቸው ራዕይ ወይም ሃሳብ ምን ነበር?

ዶ/ር አደዱ: ትልልቅ መጽሐፍትን መርጦ መተርጎም፣ ይሄን ነበር የሚፈልገው

ጭረት: ለመተርጎም የሚመርጧቸው መጽሐፍት ምን ዓይነት ነበሩ? ለምንስ ነበር የሚመርጧቸው ?

ዶ/ር አደዱ: የሚገርመሽ እኔም ጠይቄው ነበር፣ ምንድነው የሚማርክህ ለመተርጎም ስለው፣ ባዮግራፊዎች ወይም ስብዕናን የሚያስተካክልና የሚቀርጹ፣ አንዴ አንብበሽ ተገርመሽ የምታስቀምጪያቸው ሳይሆኑ የቱ ጋር እንደሆንሽ ራስሽን የምትጠይቂባቸው፣ የምትመራመሪባቸው ከስብዕና ግንባታ ጋር የተያያዙትን መተርጎም ይፈልግ ነበር።

ጭረት: ስብዕና ግንባታን ካነሳን ከአባታችሁ የህይወት መንገድ እናንተ ለራሳችሁ ምን ወሰደሰችሁ? በእናንተ ህይወት ውስጥ ያበሩት ነገር ምንድነው?



ዶ/ር አደዳ: እኔ ጋር አሳርፏል የምለው ቅድሚያ ንባብና መጽሐፍትን መውደድ ነው ከዚህም ጋር ተያይዞ ከባለቤቴ ዶ/ር አብነት ስሜ ጋር ሆነን በቤታችን ከ5ሺ በላይ የመጽሐፍት ስብስብ አለን እነሱም በባለሙያ የተሰደሩ ናቸው ይህም የአባቴ መልካም ብርሃንን ለማስቀጠል ነው እንዲሁም ባለቤቴ የጻፋቸውና የታተሙ አምስት መጽሐፍት ላይ በአርትኦት ሰራ ሰርቻለሁ። በተጨማሪም ትዕግስትን፣ ነገሮችን እንደአመጣጣቸው መመለስን፣ ሰዎችን አብዝቶ መረዳትን ወስጃለሁ።

ወ/ሮ ተዘሩ: አባታችን እጅግ መልካም ሰው ነበረ፣ የሞቀናበት ዓይነት ምነው የሱ ልምድና ጸባይ የእኔ በሆነ የምለው ነው፣ ከእርሱ ሰው መውደድን ተምሬያለሁ እንደውም ሁሌ የሚለን ነገር አለ እኔ አባታችሁ ምንም የለኝም ግን ስሜን ጠርታችሁ የትም ማደር ትችላላችሁ ይለን ነበር አውበትም መልካም ሰራው አኑሮናል፣ አይቼዋለሁም እንኔም ቢቻለኝ መልካምነቱን ብወስድ እመኛለሁ።

ጭረት : የአባታችሁ የመጽሐፍ ስብስቦች የመለገስ ሀሳቡ እንዴት መጣ?

ወ/ሮ ተዘሩ: እንዴት መሰለሽ የሆነ ቀን መጽሐፍ ተራ መጽሐፍ ሊገዛ ይሄድና የአንድ የድሮ ወዳጁ የገዛቸው መጽሀፍት ቤተሰቦቹ ካለፈ በኋላ ሸጠዋቸው መጽሀፉን ሲገልጠው ባለው ቲተር ይለየዋል እናም አንድ ለማስታወሻ ገዝቶ እያዘነ ቤት ይመለስና የእኔን መጽሐፍት ማበርከት ነው የሞፈልገው አለኝ፣

እኔም በህይወት እያለ ወደ መጨረሻው አካባቢ የፈለገውን ላደርግለት ብዬ ነበር ግን ነገሩ እሱ ካረፈ በኋላ ሆነና ሱራፌልን ከBook for all ደውዬ አገኘሁትና ጨረታ አወጣን ከዛም የወጣውን ጨረታ የተለያዩ ተቋማትና ት/ቤቶች ተሳተፉበት እኛም በወጣው መስፈርት መሰረት መዘነን እና አወዳድረን ለሳንኮፋ የአንባብያን ማሕበር ለመለገስ ወሰንን፣ ከዛም ከቤታችን ሸክፍን ወደ ጎንደር ለሚያደርሰው ልጅ በአደራ አስረከብን፣ ትልቅ ሀዘን ትልቅ ደስታም ነበር፣ ስልሽ መጽሐፍቱ የአባታችን ጓደኞች፣ ከእኛ ቀጥሎ ልጆቹና ህይወቱም ነበሩና በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉን ጠብቀን በአግባቡ መስጠታችን ደግሞ ዕረፍት ነበር።

ጭረት: በእውነት ስለነበረን ቆይታ ከልብ እናመሰግናለን፣ የአባታችሁ ህይወት ለሁላችንም ትልቅ ትምህርት ነው ።ጭረት መጽሔት በሳንኮፋ አንባብያን ማኅበር ስም ጋሽ ጎይለሥላሴ፣ በመቀጠልም እናንተን እንዲሁም መጽሐፉን በመለገስ ሂደት ውስጥ የነበረውን ሱራፌልን(Book for all) እንዲሁም እንደ ሳንኮፈ ጨረታውን የተሳተፉት ሁሉንም የሳንኮፋ አባላት ታመሰግናለች ፣ በመጨረሻ የሞትሉን ነገር ካለ እንስማና የነበረንን መልካም ቆይታ እናገባድድ

ወ/ሮ ተዘሩ: ቅድሚያ እናንተንም እናመሰግናለን፣ መጽሐፍቱን እግዚአበሔር በፈቀደልን ጊዜ መጥተን ብናያቸው ደስተኞች ነን፣ እናንተም በእንክብካቤ ያዟቸው ነው የሞንለው ፣ ሰላም ቆዩልን።

> ከቤታችን ሸክፍን ወደ ጎንደር ለሚያደርሰው ልጅ በአደራ አስረከብን፣ ትልቅ ሀዘን ትልቅ ደስታም ነበር፣ ስልሽ መጽሐፍቱ የአባታችን ጓደኞች፣ ከእኛ ቀጥሎ ልጆቹና ህይወቱም ነበሩና



ትናንት ወይስ ነገ

ዛሬከጓደኞቼጋርልንገናኝየተቀጣጠርንበት ቀን ነው። ቀኑን ከሳምንት በፊት አቅደነው ስለነበር በሰአቱ ለመድረስ ሁላችንም ከቤት ወጣን። እኔም ታናሽ ወንድሜ አምጭልኝ ያለኝን ነገሮች ጭነቅላቴ ላይ እየፃፍኩ ጉዞዬን ወደ ታክሲ መያዣው አቀናው።

ጉዞው አጭር ቢሆንም በመንገዴ ላይ የተለመዱ ፊቶች፣ የሰላምታ ፈገግታዎች ፣ እንዲሁም ምነው ባልወጣ! የሚያሰኙ ግልምጫዎችን አስተናግጃለው።

ቀኔን በፀሎት መጀመሬ የእርጋታ ስሜት ቢሰጠኝም ጓደኞቼን ከረጅም የእረፍት ጊዜ በኋላ ላገኛቸው መሆኑ ያሳደረብኝ የጉጉት ስሜት አመዝኖ ይታያል።ነገር ግን ምንጩ ከየት እንደሆነ የማላውቀው፣ የሰዎችን ቀልብ የሚሰርቅ አንዳች ስሜት ይነበብብኝ ነበር።

አካሄዴ አንድ የህወትን ቁልፍ በእጇ እንደያዘች ፣ ገፀ በረከቷን ለአለም ልትሰጥ የወጣችዋን ጮራ ይመስል በፍንደቃ የተሞላ ነበር። እንዲሁ ያለ ምክንያት...አለ አይደል.. በገዜው ተፈጥሮ ሚዛኗን ወደኔ ያደላች መስሎ ይታየኝ ነበር። ባጠገቤ የተሰለፉ ዛፎች ሳይቀሩ ባለፍኳቸው ቁጥር ከወገባቸው ዘንበል ይሉ ነበር። የምራመድበት የመሬት ንጣፍ ሳይቀር የቀይ ምንጣፍ መስሎ አረማመዴን ቄንጠኛ አርጎታል። እንዲ ያሉ ስሜቶች ከየት እንደሚመጡ ባላውቅም አልፎ አልፎ አስተናግዳቸዋለው። ምናልባት የህይወትን በጎ ነገር ብቻ አይተን በሚኖረን ከልብ የመነጨ ምስጋና አለም ምላሿን እያሳየችን ይሆነናል።

የታክሲው መያዣ ጋር ስደርስ እና እንደማንኛውም ሰው በፀሐይ ተቀቅዪ ግፋ ሲልም ተጋፍቼ ታክሲ እንደምይዝ ትዝ ሲለኝ ይሄስ የህይወት ምላሿ ነው ብዬ ፈገግ አልኩ። የተወሰኑ የስልክ ጥሪዎችን አስተናግጄ ስጨርስ ታክሲዎቹ ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። የሜክሲኮን ታክሲ አጥብቄ ስፈልግ የካሳንቺስ ታክሲዎች ተክተልትለው የሚመጡት ነገር የትዕግስት ጀረጃዬን ለፈትነት ይመስላል። ትዕግሥተኛ ነኝ ብዬ አፌን ሞልቼ ባልናገርም ለትዕግስት በቂ ነው ብዬ የማሰበውን አድል አሰጣለው።

"አንድ ሰው ሜክሲኮ ፣አንድ ሰው ሜክሲኮ.." ተመስገን ! ረዳቱ በመሰኮቱ ጭንቅላቱን አውጥቶ ሲጣራ አይኑ ከኔ አልተነቀለም ነበር። " ነይ ነይ እናት ሜክሲኮ ነሽ ግቢ ግቢ " አለኝ ። ወይ አምላኬ !...ከዚ ሁሉ ሰው እኔን ብዬ ወደ ታክሲው ገባው። ታክሲው ሞልቶ ስለነበር ሶስተኛ ወንበር ላይ ሶስተኛ ሆኜ እንድቀመጥ ረዳቱ ጠቆመኝ። እኔም ወደቦታው ሄድኩ ከዳር የተቀመጠው ቀይ ረጅም ልጅ " እግሬ ረጅም ስለሆነ መጎል መግባት አልችልም" አለኝ። ቁመትም ለካ

መሐል መንገድ ላይ ደርቄ ቀረው moment of realization

ያለቦታው ሲገኝ የራሱ ተግዳሮቶቹ አሉት ብዬ መጎል ገባው። ወዲያው ፀፀትኝ። ሊፈነዳ እንደደረሰ ቲማቲም መታጨቄ ያሳዘነው ረዳት ቦታ ለቀይረኝ ወሰነ። "ነይ እዚ ጋር ተቀመጪ" ብሎ በሰሙ ወደ ተሰየመለት ወንበር ጠቆመኝ። እንደ ሳንዴች ከከበቡኝ ሰዎች ተነስቼ በረዳቱ ወንበር ላይ በመቀመጥ የማገኘውን ነፃነት ሳስብ ተነስቼ ቦታ ለመቀየር ጊዜ አልወሰደብኝም ነበር። በመሰኮት የሚገባው ንፋስ በሀሳብ ማዕበል ለያቀዝፈኝ ሲል ረዳቱ "ሒሳብ" አለ። እጇ ላይ ያለውን 50 ብር እና ስልኬን ተመልክቶ " እናት ዝርዝር የለኝም ግን ችግር የለውም ስትወርጂ እናዘረዝረዋለን ደሞ ስልክሽን በቦርሳሽ አርገው እንዳይሰርቁሽ" ለተሳፋሪዎቹ የሚጨነቅ ረዳት



ስላጋጠመኝ ገርሞኛል።

ምቾቴ ያሰጨነቀው ይመስል በሰስት ያየኛል። እስከዛሬ ድረስ ረዳት ሲባሉ የሸፈሩ አጋዥ መሆናቸውን ለመግለፅ እንጂ መች የተሳፋሪ መሆኑን አወኩ። ታዲያ ረዳቱ ማለቴ ረዳቴ ቁጢጥ ብዬ መቀመጤ ምቾቴ አሳሰቦት ጋቢና ያለውን ሰው አስጠግቶ እንድቀመጥ ጋበዘኝ።

የጋቢናውን ምቾት ከጭነቅላቴ በፊት ሰውነቴ ገብቶት ትዕዛዝ ሳይጠብቅ ተነስቶ ጋቢና ገብቷል። የጋቢናውን በር ሰዘጋ ረዳቴ ቀረጠፍሽኝ ብሎ እሪ አለ ።...ወይ ጉድ.. የታለ እና እጄ ብዬ ግራ ተጋባው፣ ዞርም ብዬ ሰያስብልኝ ለነበረው ረዳት ..ወይኔ !ይቅርታ! ተረፈ እጅህ እያልኩ ሀዘኔታዬን ገለፅኩለት። ቆይግንእንዴት? ግራገብቶኛል ። ጥያቄው የተመለሰልኝ ትንሽ እንደቆየን ከታክሲው አግለብልበው ሲያስወጡኝ ነው "ለምንድነው ምወርደው ??" አልኩኝ እንደ ሀይለኛ... "ትራፊክ ስላለ ነው እናት ...እዛ ጋር አልፌ እቆማለው ትመጪለሽ " አለ ሹፌሩ። ሳላንገራግር ወረድኩ ። ታክሲው ተወነጨፈ ።መሐል መንገድ ላይ ደርቄ ቀረው moment of realization ይሉታል። ስልኬን እንደተበላው እያወኩ ነበር ቦርሳዬን ከፍቼ የረጋገጥኩት ። እነደ መሮጥም አረገኝ እያየሁት ባደ ሜዳ ላይ ትቶኞ ሄደ። ልቤ ተሰበረ! የስልኬ መጥፋት ሳይሆን ብቻዬን መቅረቴ አስከፋኝ። ባጓ ጥጓት እንደ ሄደች ሴት። በሞትወደው ፍቅረኛዋ እንደተከዳች አፍቃሪ ከፋኝ ። የሞን ማለቃቀስ ነው ቆፍጠን በይ ብዬ ራሴን ሰበሰብኩና ታርጋውን ለመያዝ ሞከርኩ ታክሲው ተወንጭፋል እኔም የሞት ሞቴን ሳያመልጠኝ ታርጋ ቁጥሩን ለመያዝ ሞከርኩ። አይይ!! አመለጠኝ!

ወደ ኋላ ልመለስ ወይስ ወደ ፊት ልሂድ ግራ ገባኝ አስፓልቱን ልሻገር፣ አደባባዩን ልዙረው ፣ ቆይ እግረኛ ነኝ ወይስ መኪና? ከራሴ ጋር ማውራት እንዳለብኝ ገብቶኝ ቆምኩኝ ። ከፌቴ ያለውን የማላውቀውን መንገድ ልከተል ወይስ የመጣሁበትን መንገድ ይዜ ወደ ቤቴ ልመለስ ጥያቄ ሆነብኝ።

መነሻቸው የተበላሹ ነገሮች መድረሻቸውን ማስተካከል ከባድ ነው። አንዳንዴ ወደ ኋላ ተመልሰን ማስተካከል ያለብንን ነገሮችን ሀ ብሎ መጀመሩ ስለሚያሰፈራን የተበላሸውን መንገድ እየተጓዝንበት ለማስተካከል እንታክታለን። ልፋት ብቻ ይሆናል። ሀይላችንን መሰረቱን ለማስተካከል ብናውለው ኖሮ ምንአልባትም ጉዞአችንን በፈተና የተሞላ አያደርገውም። ወደ ኋላ መመለስ ሳይሻል አይቀርም። ወደ ቤት በማደርገው ረጅም የእግር ጉዞ ፈተና የሆነብኝ መንገዱ ሳይሆን በጭነቅላቴ የሚመላለሱ ሀሳቦች፣ በመላው ሰውነቴ የሚጎርፉ ስሜቶች ናቸው። ቆይ ለነሱስ ማነው ትራፊክ ሆኖ የሚያስተናግዳቸው ። ውረዱ ውረዱ ብዬ አላወርዳቸው ነገር ተጣብቀውብኛል። አንዴ "ተመስገን አምላኬ በህይወት መትረፌ ራሱ ቀላል ነገር አይደለም!!" አላለው ከዛም "እነዚ የማይረቡ ሰርተው አይበሉም!!"

" እሺ ስልኬስ "

መቼስ ከስልክ ጋር ያለንን ቁርኝነት መግለፅ ከባድ ነው..

"ቢያንስ ተንከባክበው ነው የዘረፋኝ."..... "እነዚ ሌቦች!.."

ንዴት! ተሰርቄማ አልቀራትም ብዬ ሳልጨርስ የሰፈራችን ፖሊስ ጣቢያ ደረስኩ። ላመልክት እንዴ ? ታርጋ ቢጠይቁኝ ከ0 እና 1 ውጪ የያዘኩት ማስረጃ የለኝም ግን experiance ይሆነኛል ብዬ ገባው። የፖሊስ የምርመራ ስራን ሳስብ እነ CIA FBI ያየኋቸው የወንጀል ፊልሞች ድቅን አሉብኝ። ኦ ምን አልባትም ስልኬን ሊያገኙት ይችላሉ የሚል እምነት አደረብኝ እና ገባው። ውሳኔ ልክ እንዳልነበር የገባኝ ከ2ሰዓት ትዕግስት አስጨራሽ የፖሊስ ጥያቄዎች በኃላ ነው። የ3 ደቂቃን ወንጀል 8 ወረቀት የፈጀ ትንታኔ ሲሰጠው ሳይ ... መቼ ሐኪሞች history ይፅፍሉ ብዬ ተገረምኩ። ከዘረፍው በላይ ከፖሊሱ ጋር ያሳለፋኩት ቀለ መጠይቅ ወንጀል መስሎ ታየኝ። እንዴ እኔው በተዘረፍኩ እኔው በተበደልኩ 2 ሰ ዓት ሙሉ ማብራሪያ ስሰጥ መዋሌ አልቅሺ አልቅሺ አለኝ። ጨረሰ ስል .."የረዳቱ ሱሪ ምን ቀለሞ ነበር".. .."በአማካኝ ስንት ሰዓት ነበር ወደ ጋቢናው የገባሽው"...."ፊቱ ላይ የነበረው ስሜት ምን ይመስላል"....." ቦታው ፣ቀለሙ፣ መጠኑ፣ ብዛቱ፣ ሰዓቱ፣ ሁኔታው .... "


እረ ምናለበት በደረቁ ባጠይቀኝ እንደው ውሀና ደረቅ ኩኪስ ቢያቀርብልኝ አይ.. ከጥያቄው በላይ የተፈታተነኝ የፖሊሱ ቀስታ ነው። ቃል በቃል የልኩትን ፅፎ እንዲጨርስ 3 ጊዜ እደግሞስት ነበር። ትዕግስት ሆይ ወዴት አለሽ ? ስለምን ተውሽኝ ማለት አሁን ነበር።

ኤጭ! ብዬ ጥዬው ልወጣ እልና ደሞ ወንጀል ቢሆንስ? እረ በሰላሞ ወደ ቤቴ ልሀድ! ብዬ ጠበኩት። ትዕግስቴን እንዳለቀ የገባው ይመስል ጨርሰናል ስንደውልልሽ ትመጪልሽ አለኝ። አመሰግናለሁ ብዬ ወጣው። ተመስገን!! አንዴ እግሬ ይውጣ እንጂ አይለመደኝም experience እንደሆነ በቂ አግኝቻለው እያልኩ ወዳ ቤት የሚወስደኝን መንገድ ጀመርኩ። ከሱቅ አጠገብ ስደርስ ወንድሜ አምጪ ያለኝን ገዝቼ እቤት ገባው ።ፊቱ ላይ የነበረውን ደስታ ሳይ ያሳለፍኩትን ቀኔን አሰረሳኝ ። ህይወት ቀላል ናት እንዴ? ብዬ ጠየኩ። ለእንዳንዱ እንዴት ከረሜላ ቀኑን ታሳምረዋች። እጄ ላይ ስልክ እንደሌለ ሳስተውል እንግዳ ነገር ተሰማኝ። የለም! በቃ ተቀበይው! አልኩት ራሴን። ስልክ በስልክ እንደሚተካ አውቃለው። ለእንዳ ወዳጄ ስነግረው" በአዲስ አመት አዲስ ስልክ ሊሰጥሽ ነው ለበጎ ነው" ብሎኝ ነበር።

የድሮ ስልኬን በመርሳት እና አዲሱን ስልኬን በመልመድ መካከል እንዴት ደስ የማትል ስሜት አለች።

ቆይ መቀበል ያቃተን የቱን ነው ?ያለፈውን ውብ ገዜ መርሳት ወይስ የሚመጣውን ያልታወቀውን መጠበቅ? ሁሉም በገዜው ውብ እንደሆነ አምናለው ግን የነገው ውበት ከትናንት ውበት ጋር አይወዳደርም። አዲስ ነገር ስለሚያስፈራን ሁሌም ትላንታችን ከነገ የበለጠ መሰሎ ይሰማናል። አዎ በጣም ጥሩ ቀናት ትላንት አሳልፈን ሊሆን ይችላ፣ ትላንት በጣም ጥሩ ሰዎችን ተዋውቀን ለሆን ይችላል ግን በነገ ውስጥ የሚገኘው ጥሩነት ብቻ ሳይሆን ነገ አለመታወቁ በራሱ ውበት ይሰጠዋል ። የመኖር ድፍረት እና ጉጉት የበቀለው ነገ ከሚያመጣው አለመታወቅ ነው።

በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ብሩክታዊት መርሻ



PHOTOGRAPHY

ፎቶዋቼ መጽናናየቼ ናቸው።
That's how much photography is powerful.
The wisdom is beyond freezing a
moment, one can share the emotions behind the lens.
Its like memory in a frame

ሊት ጀፈርሶ







Pitfall

And so I thought I was done
No more escape no more run
Say won't be playing with blade
I will be all love no more hate
Healing my wound loving my scars
Kissed goodbye the monster
Lurking around the corner
Tucked it away under my bed
And hushed the demons
Pearing to my head
But then,
Just a sip of your dark soul
And I am all the things I said
I won't . . .

Skyblue



አህቱ

ቤተ-መጻሕፍት

በእንዳለ መኮነን

እንዳለ መኮነን የመጀመሪያ ድግሪውን ከመቀለ ዩኒቨርሲቲ በሕግ የተመረቀ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ አቃቤ ሕግ ሆኖ በመሥራት ላይ ይገኛል፤ በመቀለ ዩኒቨርሲቲ ፍኖተ አዕምሮ የተሰኘች ቤተ መጻሕፍት ከወዳጆቹ ጋራ መሥርቶ ለዓመታት አገልግሎት ሰጥታ አሁን ቤተመጻሕፍቷ ጠፍ ሆናለች። ትውስታውንና ሂደቱን በመጠኑ እንዲህ ከትቦልናል መልካም ንባብ።



ፍኖተ አዕምሮ

ሰዓት እና ቀኑ የገዜን ድር ይዞ ይተረትራል። ሰው ያደገ ሲመስለው ገዜው ግን እየመሸ ነው። ካለው ላይ እየተጠቀመበት በባንክ እንደተቀመጠ ገንዘብ ወይም በአራጣ እንደተሰጠ ሀብት የማይወልድ እናራሱን የማይተካው የሰው ልጅ ዕድሜ በነገ ተስፋው ውስጥ ይመነምናል ። የዛሬው ጨዋታ በትውስታ ምዕራፍ በትንሹ ፈቀቅ ብዬ በደም ላብ እና በወዝበ የወዘ እንጥፍጣፊ ላይ ስለተመሰረተችው እና በሩቅ አልማ ህልሚ አጥንት እንዳረገዘ ወላድ ከዛሬ ነገ ይወለድ ይሆን በሚል የተሰፋ መንገድ ስለተመሰረተችው ስለ ፍኖተ አዕምሮ የንባብ ማህበር እንጫወት። ከስምንት አመት በፊት የብሔራዊ የ12ኛ ክፍል ብ,ሔራዊ ፈተና ወጤትን ተከትሎ እንደማንኛው የድሃ ልጅ ያሉኝን የገላ መሸፈኛ ጨርቆች ሸምቀቆ ባለው ከኩርቱ ፌስታል በማይጠነክር ለእንገቴ በታች ለሆነው ህልውናዬን በሶ እና ቆሎ እንዲሁም ከእንገቴ በላይ ላለው እና ለህልውናዬ መሰረት ፡ የሀሳብ አክናፍ ከሰማይ አዕዋፍ ከሚበሩበት በላይ ለሚያበረኝ ከገዜ እና ቦታ አስራት በኢትዮጵያንዝም እምቢተኝነት ነጻ የሚወጣኝን ከመምህራኖች እና ከወዳጆች ከቀረምኳቸው ምርጥ ምርጥ መፃህፍት መካከል የኩርቱያ ታላቅ እስከሚችለው አጭቄ ነበር ከአዲስ አበባ 783 ኪ/ሜ በሰሜን አቅጣጫ በወቅቱ ዝነኛ በነበረው ሰላም ባስ ለአመታት ስሰበው የነበረውን የአዲስ አበባን የአየር ሽፋታ ከሌሊቱ 11፡30 ነበር ሹልክ ብዬ ከጓደኜ እናከየኒቨርስቲ ተጋሪዎቼ ጋር ከአስመራ በኮረጀችው ሰሜናዊት ኮከብ ስለተባለላት መቐለ የከነፍኩት። መቐለ ከአጼ ቴዎድሮስዋ ጎንደር የንግስና ዘፋን ወራሽነትን በአፄ የሐንስ አማካኝነት ያገኘት ከተማ ናት ። ከአዲስ አበባ ጎንደር እና ከአዲስ አበባ መቐለ የ50 ኪ/ሜ ብቻ ነው ልዩነታቸው ።
ይህች ውብ ከተማ የአጼ የሐንስ መናገሻ ከተማም ነበረች ። አሁን ላይ የትግራይ ክልል ዋና ከተማ ስትሆን በሰባት ክፍለ ከተሞች የተዋቀረች ናት። በአየር ንብረትዋ ከፈል ሙቃታማ ይላታል የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ በዘገባው የከተማዋ ነዋሪ ግን ከመስከረም እስከ የካቲት ከባድ ተብሎ የሚገለፅ ነፋሳማ ሲትሆን ከየካቲት እስከ ሰኔ ደግሞ ሙቀታማ ነው። እንደ አብዛኞቹ ኢትዮጵያ ክልል ከተሞች የመቐለ ውሃም ጨዋማ ነው። ይህ ሁሉ ግን በመቐለ ለኖረ ሰው ከልቡ ገብተው አይጎረብጡትም ። እኔ ወደዚች ከተማ ለመጀመሪያ ገዜ ብቅ ያልኩት መስከረም 21 ቀን 2008 ዓ/ም ከምሽቱ 3፡30 ነበር የመቐለ ዩኒቨርስቲ የህግ ተማሪ የሚል የማዕረግ ካባዬን ደርቤ መቐለ ከተማን ከእንዳየሱስ ወይም አሪድ ተብሎ ከሚጠራው የከተማዋ ጫፍ ሆኜ በሚሞዘገዝገው ባስ ውስጥ ሆኜ ቁልቁል ነበር ያየኋት።

ላይ የትግራይ ክልል ዋና ከተማ ስትሆን በሰባት ክፍለ ከተሞች የተዋቀረች ናት። በአየር ንብረትዋ ከፈል ሙቃታማ ይላታል የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ በዘገባው የከተማዋ ነዋሪ ግን ከመስከረም እስከ የካቲት ከባድ ተብሎ የሚገለፅ ነፋሳማ ሲትሆን ከየካቲት እስከ ሰኔ ደግሞ ሙቀታማ ነው። እንደ አብዛኞቹ ኢትዮጵያ ክልል ከተሞች የመቐለ ውሃም ጨዋማ ነው። ይህ ሁሉ ግን በመቐለ ለኖረ ሰው ከልቡ ገብተው አይጎረብጡትም ። እኔ ወደዚች ከተማ ለመጀመሪያ ገዜ ብቅ ያልኩት መስከረም 21 ቀን 2008 ዓ/ም ከምሽቱ 3፡30 ነበር የመቐለ ዩኒቨርስቲ የህግ ተማሪ የሚል የማዕረግ ካባዬን ደርቤ መቐለ ከተማን ከእንዳየሱስ ወይም አሪድ ተብሎ ከሚጠራው የከተማዋ ጫፍ ሆኜ በሚሞዘገዝገው ባስ ውስጥ ሆኜ ቁልቁል ነበር ያየኋት።

መቐለ ዩኒቨርስቲ መግባቴን ያረጋገጥኩት በትልቁ መቐለ ዩኒቨርስቲ የህግ እና ሰነ መንግስት ኮሌጅ በሚለው የሚል ከበሩ አላናት ላይ እንደጅብራ በተፃፈው ሰር ዘልቄ ወደ ውስጥ ሰገባ ነበር ያወኩት።

የሞዝገባ እና አውደልዳይነት ገዜዬ ሲያቃ የያዝካትን የመፅሐፍ ጥርኝ አገላበጥኩ ወዳጆቼንም ጠየኩ ነገር ግን አሁንም በቂ አልነበረዉም ከፍ ሲልም በወቅቱ አንድም መፅሐፍ በቀን ሃምሳ ሳንቲም የሚያከራይ ከየነቨርስቲው ወጪ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን የመፅሐፍ ኪራዬ ከአንድ ወር መሻገር አልቻልም ነበር። ለምን የኪሴ ሞች በተማሪ ዳማከሴ የሚቻል አልነበረም እናም የየነቨርስቲው ቤተ መፃህፍት ብሔድም አፌን በፈታሁበት እና ቃላትን እንዳሻኝ በማውጠነጥንብ አማርኛ የተፃፉ መፃህፍት ለየነቨርስቲው መካን ነበሩ እና መቅለ የነቨርስቲን የሚያክል መካነ አዕምሮ ለተራቡ አይኖቼ ማረፊያ አሳጡት ይልቅ ቤተ መፅሐፉ ከጥግ እስከ ጥግ ከእኔ ጋር በጠላትነት የምንፈላለግ በሚመስለኝ በእንግሊዘኛ በተፃፉ መፃህት ተመልቶ ያቃትታል። ይህም እንዳለ ሆኖ በዚህ በኩል ደግሞ እንደ 1960ዎቹ ትውልድ አንዳች በጎ ነገር ሰርቶ የታረክ አሻራን ማስቀመጥ እንዳለብን በተማሪዎች መመገቢያ ታህሳስ ወር ከምሽቱ 1:00 ለ30 ደቂቃ የንባብ ማህበር መመስረት እንዳለብን ቃልአብ ይርጋለም. ሩሃማ አሸቱ፣ ሀቤከ ሰዩም፣ እንዳለ መኮነን፣ አብዱራህማን ሻሎም፣ ዘላለም አበራ፣ ቃልኪዳን እና ጋቢሳ ያሲን ጋራ በመሆን ከስምምነት ላይ የተደረሰው። በወቅቱ ለመነሻ እንዲሆን ሁሉም መስራች የነበሩት አባላት አምስት አምስት መፃህፍት ለሚመሰረተው ቤተ መፃህፍት በመስጠት ነበር ትግሉ የተጀመረው።

እናም ተማሪው የአንደኛ ሴሚስተር እረፍቱን ከወዳጅ ዘመዶቹ ጋር በወደደው ቦታ ሲያሳልፍ የዚህ ማህበር ጠንሳሾች ግን አላማ አላቸው እና ከጦር ጎይሎች መገኛኛ ከአሰር ገዜ በላይ ደርሶ መልስ ለዛውም በእግር ።

ከለገሃር በቸርቸር ጎዳና ፒያሳ ከዛም አራት ኪሎ እና ስድስት ኪሎ፡ ፡ እሱም አይበቃ እስከ ደንቦስኮ ትምህርት ቤት የመፃፍትየልማና ዘሌዳ አውጥተን የመሃል አዲስ አበባ የነበሩ መፃህፍት ቤቶችን ስለ አላማችን ገለፃ በማድረግ እና በማሰባሰብ ስራ ላይ ነበር የተጠመድነው።

በዚህም በአጠቃላይ በአንድ ሴሚስተር ከ250 መፃህፍት በላይ ያገኘን ቢሆንም ከባዱ የነበረው ግን ይህን መፃህፍት እንዴት እናጓጉዘው የሚለው ነበር። የማያልፉት የለም እንዳለ ደራሲ እያንዳንዳች ተከፋፍለን ነበር ያደረስነው። በኋላም ማህበራችን በመቐለ የነቨርስቲ ፍኖተ አዕምሮ የአንባብያን ማህበር በሚል በ2009 ዓ/ም ሚያዝያ ወር ላይ የመጀመሪያ ኤግዚብሽን በመቐለ

በአጠቃላይ በአንድ ሴሚስተር ከ250 መፃህፍት በላይ ያገኘን ቢሆንም ከባዱ የነበረው ግን ይህን መፃህፍት እንዴት እናጓጉዘው የሚለው ነበር።

በዚህም በአጠቃላይ በአንድ ሴሚስተር ከ250 መፃህፍት በላይ ያገኘን ቢሆንም ከባዱ የነበረው ግን ይህን መፃህፍት እንዴት እናጓጉዘው የሚለው ነበር። የማያልፉት የለም እንዳለ ደራሲ እያንዳንዳች ተከፋፍለን ነበር ያደረስነው። በኋላም ማህበራችን በመቐለ የነቨርስቲ ፍኖተ አዕምሮ የአንባብያን ማህበር በሚል በ2009 ዓ/ም ሚያዝያ ወር ላይ የመጀመሪያ ኤግዚብሽን በመቐለ የነቨርስቲ አዲ ሃቂ ግቢ ወይም ካምፓስ በማድረግ ነበር ለግቢው ማህበረሰብ በነፃ መፃህፍት የማዋስ ስራውን የጀመረችው። በሰገሌ የደነቆረ ጨዋታው ሁሉ ሰገሌ ነው እንዳሚባለው ማን እንዳለው እና እንደጀመረው የማይታወቅ አንድ ጅል የከለውን አምሳ ሊቅ አይነቅስትም እና የዚህ ዘመን ተማሪ አያነብም የሚል የተሳሳተ ትርክት በይፋ ድምጥማጡን አጠፋው እጃችን የነበሩት መፃህፍት ተውሰው አለቁ። እና አውነት አያነብም ብሎ ለሚጠይቅ ቀላል አስል ነው መልሱ። ነገር ግን የመፅሐፍ ዋጋ እንደ አልማዝ በሆነበት ሀገር የነቨርስዎች በስፖንሰር ስም የፈረደባቸው ምዕራባውያን አያስፈልገንም በሚል የጣስትን የፈረደባቸው ምዕራባውያን አያስፈልገንም በሚል የጣስትን በየነቨርስቲው ቤተ መፅሐፍ ቢሞስትም ምን ጥቅም ይሰጣል። ስተማሪው ምን ጠብ የሚልስት ነገር አስ ይህን ችግር ተዘዋውሬ ባየሁባቸው የጎንደር የነቨርስቲ (ሳንኮፋዎች ምስክር ናቸው) የአዲግራት የነቨርስቲ.፣ የባህር ዳር የነቨርስቲ፣ የመቐለ የነቨርስቲ እና በተመሳሳይ በሁሉም የነቨርሰቲዎች ላይ ያለ ችግር ይመስለናል። እስከ 2010ዓ/ም ያለውን እና የተመለከትኩን ነው ማስቀመጤ።

ፍኖተ አዕምሮ ሆይ ምን ላይ ነሽ እያልን እናስብሻለን። እስራኤል በባርነት ወደ ባቢሎን በወረዱ ገዜ ሀገራቸው እስራኤልን ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ በማለት እንደተቀኙላት እኛም እንላለን ምንም ባልነበረን ሰዓት በባደ እጅ በሰው ፌት በልመና እና በብዙ መከራ ከአጭር ገዜ እስከ ረጅም ገዜ ዕቅድ በማዘጋጀት ከመቐለ የነቨርስቲ እስከ መላ ኢትዮጵያ ቤተ መፅሐፍ መሆን ተስፋ የነበራትን የበኩር ልጃችንን ባናስብሽ ..... እያልን እንቀኝላታለን።

ሰላማችሁ እንደ በርበሬ ያቃጥል፣ ፍቅራችሁ እንደ ውቅያኖስ ያጥለቅልቅ ።
እንዳለ መኮነን ነኝ ከፍኖተ አዕምሮ መስራች።
እነሆ በፍኖተ አዕምሮ መሪ ቃል ልሰናበታችሁ።
ዕውቀት አይናማ ነው ለሌሎች የተሰወረውን ያያልና።






ꓰꓞꓤꓢꓐꓕꓢ ꓰꓞꓐꓢ

ꓲꓤꓢꓐꓰꓞꓢꓕ

የነሐስ ጥበበኞች



የኤዶ ህዝቦች የሚገኙት በደቡብ ምዕራብ ናይጄሪያ በሞትገኘው ቤኒን ከተማ (ይህ ቤኒን ከቤኒን ሪፐብሊክ የተለየ ነው) ውስጥ ነው። ቤኒን ከተማ በድሮ ጊዜ የቤኒን መንግስት (Kingdom of Benin) ዋና ከተማ ነበር። የቤኒን መንግስት (ከ11ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን) በምዕራብ አፍሪካ አንሰራርተው ከነበሩ ሌሎች መንግስታት ጋር ሲነፃፀር በስልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ ቆይቷል።

የኤዶ ህዝቦች ራሳቸውን ቢኒ ወይም የቢኒ ህዝቦች እያሉ ይጠራሉ። የቢኒ ህዝቦች ለረጅም ጊዜ የቆየ ህዝቦች በመሆናቸው ሰፊ ታሪክ እና ቱባ ባህል አላቸዉ ። የአለምን አፈጣጠር ታሪክ ፣ የሰው ልጅ ነፍስ አፈጣጠር እና ወደ ዓለም መምጣት ከዕጣ ፈንታ ጋር በማያያዝ የሚነገሩ ታሪኮች አሏቸው ። የንጉሦቻቸው ተዋረድም ከፈጣሪ ፀጋ ጋር የተያያዘ ነው ብለው እንደሚያምኑ ከተለያዩ ፅሁፎች መገንዘብ ይቻላል። ስለ ኤዶ መሪዎች ፣ ስለ ወታደራዊ አቅማቸው ፣ ስለ አምልኮ ስርዓታቸው እና ህጎቻቸው ፣ ስለ ስነ ህንፃ ጥበባቸው እንዲሁም ስለ አልባሳትና ጌጦቻቸው ብዙ ማለት ይቻላል። ከነዚህ ውስጥ ጥቂቱን በሌሎች ዕትሞች የምናነሳ ይሆናል። በዚህ ዕትም በዋነኝነት ስለ ዕጅ ስራዎቻቸው እናነሳለን።



የቢኒ ህዝቦች የነሃስ ቅርሶችን እና መገልገያዎችን በመስራት ቀዳሚ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል ። አብዛኞቹ የነሃስ ስራዎች የንጉሥ እና ንግሥቶቻቸውን መልክ የያዘ ሲሆን ብዙ ጊዜ እነዚህን ስራዎች በስጦታ አበርክተዋል ። የቢኒ ጥበበኞች እነዚህን ስራዎች ለመስራት በዋነኝነት መዳብ ፣ ብረት እና የዘሆን ጥርስ ይጠቀሙ ነበር። መስራት የጀመሩት በ13ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ በኦባ አጉዋላ የንግሥና ዘመን ነው። በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ አውሮፓውያን በጀመሩት አፍሪካን የመቀራመት ጉዞ ውስጥ የቤኒን መንግስት ለጥቂት ዓመታት ሉዓላዊነቱን አስጠብቆ መቆየት ችሏል ። ነገር ግን በ1897 እ.ኤ.አ እንግሊዞች በሪር አድሚራል ሄንሪ ራውሰን መሪነት ባደረጉት ወረራ ብዙ ህዝብ አለቀ ፣ ቤቶች ተዘረፉ ፣ ህንፃዎች ተቃጠሉ ። የኤዶ ህዝቦች ጥበብ ያረፈባቸው የነሃስ ስራዎችም ተዘረፉ። ከነዚህ ሰራዎች ውስጥ ወደ 40 ፐርሰንት የሚሆኑት በእንግሊዝ ሙዚየሞች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን የተቀሩት በገዜው ለነበሩት ወታደሮች ተሰጥተዋል ።ከዚህም የተረፉት ደግሞ ለጨረታ ቀርበው ነበር። በአሁኑ ሰዓት የቤኒን ነሃሶች በጣም በብዛት የሚገኙት በበርሊን ኤትኖሎጂካል ሙዚየም እና ለንደን በሚገኘው ብሪቲሽ ሙዝየም ውስጥ ነው።

እነዚህ የነሀስ ጥበቦች እንዲመለሱ ለማድረግ ናይጄሪያውያን ለረጅም ዘመናት ጥረት ሲያደርጉ ኖረዋል። ቢሆንም የተመለሱት የነሀስ ስራዎች በጣም ጥቂት ሲሆን እንግሊዝ ደግሞ ምንም እንኳን ለመመለስ ተስማሞታ የነበረ ቢሆንም የመለሱት ግን በቁጥር በጣም ትንሽ ነዉ ። ናይጄሪያ ግን አሁንም ጥረቷን ቀጥላለች።




ሀሰሳ

.....

.....

በቃላቴ
ሰርጣ ሰርጡ
ውስጣ ውስጡ
ተዳሰሰ ሰውነቴ
ኳይ ወግ እቴ!
በብዕሬ
ተከቺተ በሌበሬ
ተበረበረ መኖሬ
"ከርሞ ጥጃ ኣዶሮ ጥሬ"
ቢሆንም ቅኩ
ጣቶቼ ኣይሰሐቑም.....
ብዕሬን ታቅፈው
በወረቀት ፌት ላይ ይንቀዋለላኩ
ቃላት ይፅፉ!
ጣቶቼ ኣይሰሐቑም.....
ብሩሼን ታቅፈው
በሸሌው ገፅ ላይ ቀለም ይቀባኩ
ስዕል ይስላኩ!
በህይወቴ ንዳ ይመላለሳኩ
ይንገላወዳኩ
ኳንዴ ይፅፉ.....
.....ኳንዴ ይስላኩ
ከትላንት ዛሬ ከነገ ማህደር
ትርጉም ያለሳኩ
ያተሌምሳኩ
የለም እንጂ ቅኩ!
✍ ሊሾኬት ሞገስ ✍
[ሊሾ ዘሁሩታ]
13/1/2016 ኩ.ም
ጎንደር



SCRIBBLES

REBECCA YARED

"May we think of freedom, not as the right to do as we please but as the oportunity to do what is right."

- Peter Marshall -

Language is not expressive enough. It is tough to find words that fit into their intended meanings. They are either too 'large' or too 'small' to describe feelings and notions, or the other way around. Take word as 'freedom' for instance. The word does not give off any sense of constraint on how one acts or thinks. It elludes one to assume that there is a certain state of being where one an be 'free' of limitations, necessities and coercion, a state where one is powerful to do whatever one desires. This is the sense that we strive to ahieve when we seek freedom in its wholesome definition. The truth of the matter usually hits us late. Even our human nature does not allow us 'to be free'. We have needs that make us subservient to our own body, to say the least. We can not simply be free enough to not eat regularly, sleep very little every night or not have anything to wear. We would have to deal with harsh consequences to win over our bodies' urges. Looking further, we can not bear to only look after ourselves while living in a community. We have loved ones around us who we respect and love enough to incorporate their thoughts and desires into our own. We have bosses we need to obey, clients we need to please, governments whome we live under.



T h e moment we attempt to leave these aside, there are consequences ranging from getting a bad look from others to a death sentence. There will always be a governor outside of us that we hearken, whether we will it or not; we cannot all be leaders, some of us have to be led. We cannot always get to choose 'freely'. It won't always be essay type questions, a lot of times we will get multiple choice types and only get to choose among the options that we are given. It all comes with outcomes that we cannot fully control. Moreover, it seems that the concept of freedom, on an individual level, is an attempt from social and religious etiquettes that have held communities in order for centuries. This brings us to deduct that freedom, in reality, is far more complex than the term and concept reflect. The search for the actual definition of freedom in our own worlds continues, but as one grow older one may find it to be more of a not-so-free concept.

"Freedom is choosing your responsibility. It is not having no responsibilities, it is choosing the ones you want."

- Toni Morrison -


ቀኑ

የሁለታችን ቀን
ቀኑ፣ቀንህ፣ቀኔ
ካንዳች ካልጠቀመም
ወደ ላንተ፣ ወደ ለኔ
ስለዚህ...
ካንጨለሰ ቀናችን
ካደታደ ላጋችን
እቤሩዋለሁኝ እንዳ
ትላንታችን

ኬሊያስ

ዶክመንተሪ ፊልም

ማማ በሰማይ



ያትውልድ እንደ ቀልድ ረገፈ፣አጥፊ፣ጠፊ፣እውነተኛ፣ሀሰተኛ ሳይለይ ብዙ ወጣት አለፈ። አንድም ለቆመለት አብዮት አንድም በቆመለት አብዮት። ይህ መፅሐፍ የ1960ና70 የወጣቶችእንቅስቃሴ ውስጥ ከሞልመላው አንስቶ፣ተጋድሎው ኋላም እስከ ፍጻሜው ያለውን የጸሐፊዋን ህይወት ተፈራ ያልታሰበ የወጣትነት መንገድ፣ሀሳብ እና ዕይታዎችን የሚያነሳ በተለይም ደግሞ የአብዮትን ነገር፣ ንድፈ ሃሳቦችን እንደ ሀሁ እያስቆጠረ ስላስተማራት፣ ራሷን ለሰጠችለት ህቡዕ ቡድን(ኢሐፓ) ያስመለመላትን የፍቅረኛዋን የጌታቸው ማሩ ፍኖትና ሀቅን ራሷ ካየችውን፣በገዜያት የሰማችውን የያዘ ነው።
Tower in the sky በ2004 ዓ.ም በሚል ቅድሚያ በእንግሊዘኛ የተጻፈ፣ኋላም በ2007 በጌታቸው አንተነህ ማማ በሰማይ በሚል የተተረጎመ፣ በአንደኛ መደብ የተተረከ ባለ 386 ገጽ ታሪካዊ ማስታወሻ ነው። መፅሀፉ ምዕራፎችና ክፍሎች የሌለት ሲሆን ታሪኮቹን ለመለየት እንደ ምዕራፍ የተጠቀመችው የዛን ክፍል ሃሳብ ሊገልጹላት በሚችሉ የተለያዩ ጸሐፊያን ጥቅሶችና አባባሎች ነው ይህም ደስ የሚልና ለየት ያለ ነው። እንደ አንባቢ ይህን አካሄዷን የወደድኩት ቢሆንም የገፅ ቁጥር ካልተያዘ በስተቀር ያነበቡበት ክፍልን ፈልጎ ለማግኘት ግን አስቸጋሪ ያረገዋል ነገር ግን መጀመሪያ ጥቅሱን እንደ ዐረፍተ ነገር ጎይስ ቃል ተይዞ ከዚያም ምን ልትነግረን እንደፈለገች ለመረዳትና፣ ሃሳቧ ሲጠናቀቅ ደግሞ በቀላሉ ጥቅሶቹ የምዕራፉን አንኳር ሃሳብ ሸካፌ እንዲሆኑ ለተደራሲውና ለድርሰቷ መፍቀዷ መልካም የሞለው ነው።
የመፅሀፏንም ርዕስ ከታዋቂው ሊባኖሳዊ ደራሲ ካህሊል ጅብራል Farewell ግጥም የወሰደችው ሲሆን መጽሐፉን ለማስታወሻነት ላበረከተችለት ጌታቸው ማሩ ይሆናል ብላ ያሰበችው ነው በእርግጥም ስታነቡት ግጥሙን በርዕስነት መጠቀሟ ልክ እንደሆነ ይገለጥላችኋል፤ይህም ከምንም በላይ የወደድኩት ነው።



**“Farewell to you and the youth I have spent with you.
It was but yesterday we met in a dream.
You have sung to me in my aloneness, and I of your longings have built a tower in the sky.
But now our sleep has fled and our dream is over, and it is no longer dawn.
The noontide is upon us and our half waking has turned to fuller day, and we must part.
If in the twilight of memory we should meet once more, we shall speak again together and you shall sing to me a deeper song.
And if our hands should meet in another dream we shall build another tower in the sky.”**



ህይወት በማማ በሰማይ ውስጥ ለአብዮቱ የነበራቸው ቁርጠኝነት፣የንባብ ባህላቸውን፣የጥናት ቡድኑን፣ ራሳቸውን ለአንድ ዓላማ መስጠታቸውን፣ በዛ ወጣትነት ሀገራቸውን ለመቀየር የነበራቸውን ተስፋ፣ የህዝብን ህመም የኔ ማለታቸውን ስታደንቅ በተቃራኒው ደግሞ ያን ያህል ራሳቸውን የሰጡለትን ሃሳብ ቅራኔን በአግባቡ መፍታት ያለመቻላቸው እንዳንኮታኮተው እና በስሜታዊነት ማሰባቸውን ትወቅሳለች በዚህም ምክንያት ራሳቸውን በከንቱ ማድከማቸውን እንደውም ቦሄማን(Bohei-man) ሆኖ መኖር ይሻል እንደነበር ታነሳለች ከዛም በመጽሐፏ የመጨረሻ ክፍል ትልቁ የህይወት ትምህርቷ ጌታቸው ማሩ ያስተማራት አንደሆነና ለሰው ልጅ ህይወት ክብር መስጠትን፣መቻቻልንና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታትን እንደሆነ በመንገር ታገባድዳለች።።
ታሪኩን ሰምቶና አንብቦ ከማለፍ በዘለለ ማማ በሰማይ ስህተቶች እንዳይደገሙ የሚሰብክ ሲሆን ይህን መፅሀፍ ብታነቡት እንደምትወዱትና እንደምትማሩበት ካሰባችሁ “ዳኛው ማነው” የሚለውን የታደለች ኀይለሚካኤልን መፅሐፍ ደግሞ መጎብኘት እንዳትረሱ።።

ህይወት ተፈራን በ Mine to win (ጎሠሣ)፣ ምንትዋብ (ታሪካዊ ልብወለድ) ሥራዎቿ እናገኛታለን።።

“ማማ በሰማይ የፍቅር ታሪክ ነው።። የአብዮትም፣ የተስፋም፣ ህልምም፣ የአመጽም፣ የሽብርም፣ የመተማመንም፣ የመከዳዳትም፣ የሰቆቃና የሰቀቀንም፣ራስን በራስ የመለወጥምና የድል አድራጊነትም የነዚህ ሁሉ ሰብአዊ ረቂቅ ባሕሪያት ታሪክ ነው።።”

ካዳሩሽን ዋጪኝ

የህልም መዳፎች፣
ዳባሽ ለስላሳ እጆች፣
ህልም ካዳሩሽ መላጮች፣
ውበት ያነገቱ የሚያዜሙ ኖቶች፣
ጣቶችሽ የፃኑት፣
የባቲ! ያንቺሆዮ! የኪንባሰልን!ቅኝት፣
የልቤን ትርታ፣
የቀኔንን ትዝታ፣
የኬት ዳናዎቼን የበራን ኳ! ኳታ፣
የልቤን ውስጠ ምት ዜመኛ ትርታ፣
ተረዳተዋል መሰል ሁናነቴን ኪውቀው፣
በህልም ዓለም መንገዶ ሲጠሩኝ ና! ብለው፣
ከሚያስሱኝ ዓይኖች፣
ብሌኖችሽ መሐል፣
እሩሴን ኪያላው የኪፍቃሪሽን ምስል።
ኪንቺዮ ይገርማል፣
ለካስ ኬላ ዓለም ነሽ፣
የሩስሽ ጨረቃ ክዋክብትም ºያሉሽ፣
ለናፍቆቴ ሙዳይ፣
እዝል እና ኪሩሌይ፣
ከኪእዋኑት ዜማ መቋጠርሽ'ን ሳይ፣
በያሬዶ ዜማ ምት ገብታ ተከልላ፣
ያስብለኛል ገላ፣
"የኔ ስስ ነጠላ"፣
የጭላሽ ውልብታ፣
የጠረንሽ ኸታ፣
በቅፅበት ኸውታ፣
ኬት.ኬት እየመጣ ምሰቃየ'ው ስቃይ
ምነው.በረዘመ ያስበለኛል 'እ.ሰይ!'።

ከሚያስሱኝ ዓይኖችሽ፣
ብሌኖችሽ መሐል፣
እሩሴን ኪያላው የኪፍቃሪሽን ምስል፣
ስባዝኔ ስማለን የገባኝ በኃላ፣
የሐሴቴ ሰማይ የዳስታ'ዮ ኬላ፣
ኬላ ፍጭረት የለም ፣
ካንቺ'ም የሚኑላ፣
የኔ ሰማይ ኪዳማስ፣
የሩስሽ ጨረቃ ክዋክብትም ºያሉሽ፣
በህልሜ ዓለም ሳይቀር፣
ባላል ትመጫለሽ፣
በኪንባሰል÷ኪንቺሆዮሽ፣
ፍቅር'ሽ በፍቅሬ በትዝታ እ'ያሰርሽ፣
ህልም እንዳሰመጠኝ ሳልነቃ ሰው'ዮ'ሽ፣
ካንጀት'ሽ ኪስቀምጪኝ፣
ኪዳሩ ኪንቺሆ'ዮ ወዳ ውስጥ'ሽ ዋጪኝ፣
ተስፉ ባጣ ገላ በናፍቆት ኪትቅጪኝ፣
ºººººººººº ኪዳሩሽን! ዋጪኝ ::ºººººººº

✍ ኅገረ-ህልም✍

@ቢኒ የዳሜ ልጅ

ጠቦቭ ኾፓፐ

"One day or Day one"
ትሁት ኀይሉ
5ኛ ዓመት የኪነ ህንጻ ተማሪ

ትሁት ኀይሉ ትባላለች፣የ"Humble jewlery design"ን የዛሬ 2 ዓመት አካባቢ በኮሮና ሰዓት የጀመረች ሲሆን የታላቅ እህቷ አርአያነት፣የኪነ ህንጻ ተማሪ መሆኗና በዚሁ መስክ የዛሃ ሃዲድ(Za-ha hadid) አድናቂ መሆኗም ለፈጠራ ስራ ይበልጥ እንዳነሳሳት ትገልጻለች ። በስራዬ ውስጥ ሁሉ የቤተሰቦቼ ድጋፍ አይለይኝም የምትለው እሷ ምንም ነገር ከፈለግን እና ከወደድነው ወስነን መጀመር አለብን ለዛም "one day or day one" የሚለውን አባባል ሀሳቧን እንደሚገልጽላትና እንደምትወደው ትናገራለች።

















ይቅር

ቀጸላ

ይድረስ ለእቀቃ ሚስቴ

ለምን እንደሆነ ባላስታውስም ሁሌ እቀቃ ስንጫወት የምንሞሸረው እኔና አንቺ ነበርን።ትዝ ይልሻል ? አንዴ ትርሲት ለናቷ እኔን ሙሽራ አያረጉኝም ብላ አልቅሳ ተናግራብን! የትርሲቴ እናት ይዛት ወደኛ መጣች እና ሁላችንም በየተራ ሙሽራ እንድንሆን አስማምታን ሄደች። ከዛ ባንቺ ፋንታ እሷን እንዳገባ ተወሰነ።በጣም ቅር አለኝ።ግን እኔ ታማኝ የእቀቃ ባልሽ ዘየድኩ። እኔና አንቺ የሙሽሪት እናትናባት ሆን። ሽምግልና የተላከበት እልል ያለ ሰርግ ደግሰን በወጉ ትርሲቴን ለሄና ዳርናት።ሳስበው ያስቀኛል። ይበልጥ የሚያስቀኝ ደሞ ጎርምሰን በእኩዮቻችን ሙድ የሚያዝበት እድሜ ላይ ስንደርስ እንኳን ፤ ላንቺ የነበረኝ የስሜት ታማኝነት ነው።በሌሎች ሴት ተማሪዎች ሙድ ሲያዝብኝ የምር ነበር የሚደብረኝ።ባንቺ ሲሆን ግን...ብቻ በማፈርና በመደበር መካከል ባለው ልዩነቴ ደሞ የሚደርስብኝ ሌላ ሙድ መያዝ። ያው ከፍ ስንል እንኳ የገባቸው አብሯደግ ጓደኞቼ ብቻችንን ስንሆን ካልሆነ ሰው ፊት ስለማያስፎግሩኝ peace ነበር።

ካሳለፍናቸው ሁሉ የሞወደውን አንድ ጊዜ ላስታውስሽ የ 2004 እንቁጣጣሽ።ከዛ በፊት ላሉት ተከታታይ ዓመታት አበባየሆሽ ስትጨፍሩ እከተላችሁ ነበር።ለምን እንደሆነ፡ እንኳን አሁን ያኔም አይገባኝ። ታድያ ዓመት በዓሉ ደርሶ እያለ ተሰባስበን ስለእንቁጣጣሽና ስለአበባየሆሽ ስናወራ እማማ አለሚቱ "አንተ አታፍርም!ምኑ ሴትአውል ነው?ሆ! መች ነው ከሴቶቹ ስር ምትጠፋው ቆይ? ወይ አንድፌቱን ቀሚስ ልበስ " ብለውኝ ሲሄዱ የተያየነው መተያየት። ሁሉም ሰው እንዴት አንድ ሀሳብ ያስባል? ደሞ የለቱስት እራሳቸው ሃሳቡን ያቀረቡት እማማ አለሚቱ እንኳ አለየኝም ነበር እኮ !ጭራሽ የማነች ቆንጆ ይቺ ደሞ?ብለው አገላብጠው የሳሙኝስ!። የእውነት ግን ይቺን አስተያየት ካንቺ ጎን ቆሜ መቀበል በመቻሌ ያለሞ መንግስታት ተሰባስበው ሰለውበቴ እንደመሰከረልኝ ነው የሞቆጥረው።



ታ ድ ያ እ ን ደ ዛ ባንድ ላይ ትምርት ቤት ተመላልሰን አድገን፣ ላፍታ እንኳ ሳንለያይ እንደታላቅ ወንድምሽ ሚስጥርሽን አጋርተሽኝ፣ እንደ...ስርስርሽ እያልኩኝ አብረን ኖረን እኔ የ 12ተኛ ክፍል ውጤት መቶልኝ አንቺን ስ 11ኛ ክፍል ትምህርት ትቼሽ ኮሌጅ ልበጥስ ስል የተሰማኝ እንባ ቀረሽ ውስጣዊ እሪታ፤ ገቢ ልሄድ በዋዜማው ማታ ቻው ተባብለን ሽኝቼሽ ስመለስ ሆድ ብሶኝ መኝታ ቤት ስገባ ሆድ የባሳት እማ ተከትላኝ ገብታ "ድሮም ከኔ መለየት አይወድም አሱ" እያለች አቅፋኝ ስትቀውጠው ተገርፌ እንኳን የማላስቀሰው ልጅ እንባዬ ዱብ ዱብ ሲል አይቶ አባዬ የተናደደው ንዴት፤ ያኔ ከናንተ ክፍል ካለው ማነው ስሙ ...ስሙን ቄስ ይጥራውና ከሱ ፍቅር ያዘኝ እያልሽ ስታለቅሺ በር ዘግቼ አልበላም አልጠጣም ግን ምንም አልሆንኩ እያልኩ ስነፋረቅ ቡዳ በላው ብለው የጭስ አይነት ሲያጥኑኝ ።

ብቻ ምኑ ቅጡ! ናፍቆት የማይጠራው ትዝታ ፡የማይጠራው ብሶት የለ ።መቼስ ባይላክም የተናገሩት ያህል እንዲቀል በብዕር እንባ አድርገው ምስኪን ወረቀት ላይ እንዲ ካለቀለቁት መች ይቀልና!።

ዓመቱን ሙሉ ተቋርጦ የማያቀው የኔና አንቺ ስልክ ለእንቁጣጣሽ ግን ይለያል።ጨዋታችን ሁሉ እንደ መስክ ሜዳ በመሰከረም ይበልጡን ያብባል።ለእንቁጣጣሽ በተለየ እኔን የማስታወስ ምክንያትሽ ምንም ይሁን ምን የ2004 እንቁጣጣሽ ግን የራሷን አሻራ እንዳሳረፈች አምናለሁ። ሁሌም አልቀድምሽም፤ በፍፁም አትረሺኝም፤ ሁሌ ለመሳቅ የምንመዘውን ታሪክ ያቺ የ 2004ዓ.ም እንቁጣጣሽ ዐመታቷ በመጣ ቁጥር ሹክ ትለናለች። በወቅቱ ካልተረዳሁት የእትዬ አለሚቱ አሽሙር ፡መንገድ ላይ ለዓይናቸው አዲስ የሆንኩባቸው ጎረቤቶች ስሜን ሲጠይቁኝ ዞሬ እስከጠየኩሽ። ብቻ ከሁሉም ግን ከብዙ ገዜያቶች አንዴ የሚገኘው ያንቺ የስልክ ጥሪ ብዙ ውብ ትዝታዎችን እና ትንሽ ጭላንጭል ተስፋን ይዞ መጥቶ ጀርባዬን አይቼ ወደፊት ለመጓዝ(ባልጓዝም በቆምኩበት እንድፀና) የሚያበረታኝን፣ ሴት አንቺ ብቻ እንደሆንሽ የሚያስታውሰኝን ልዩ ጥንካሬ ስለሚቸረኝ ፤ ለኔ በአደይ ከሚሸፈኑት ግሪም ሜዳዎች በላይ ደምቄ የምፈካበት ወቅቴ ፡ከበዓላቶቼ ሁሉ ውቡ እንቁጣጣሽ ነው። ካሉኝ ነገሮች ሁሉ ደሞ ውዱ ና ክቡሩ ምን እነንደሆነ ታውቂያለሽ? ከልጅነቴ ጀምሮ ተለይቶኝ የማያውቀው ያንቺው እንቁ ጣጣሽ (በልቤ ያስቀመጥሽው ፍቅርሽ)ነው።

ያንቺው ቀጸላ

#ግለት_እና_አለት

ምነው በነገርኽኝ የከንቺርኽን ሶንበር
በ'ሳት እንዳጠርኽው
ምስኪኑን ከንቺሬን የ'ሳት እሩት ሲሆን
ዝም ብለኽ ጠበስኽው
ባንቺ መቃጠሌን እግዜር ከላይ ኻይቶ
ሰማዩ ቢያለቅስም
የጾፍ ናዳ ወርዶ ኻካኬ ቢርስም
የዝናብ ጠብታ ከከንቺሬ ኻይጾርስም
እንዴት ብሎ.... በየት ኻርጎ
ከንቺሬ ከንቺርኽ ውስጥ እንዳ ኽሉታ
መኽጎ
ማን ያውነው ሚስኪን ከንቺር
እሳት ለሞ ሲንቺሩቺር
ልቀቂኝ...
ል..ቀ..ቂ..ኝ
በቃኝ በቃኝ ተቃጠልኩኝ
እንዳ በዳይ ለምጻም ሆንኩኝ
እስኪ... እይኝ
....እይኝ....
ተቃጥሎ እንዳበቃ እንዳ ክብሬት
እንጨት
ከለሞልጥል መልኬ በከንቺርኽ ግለት
.....ያልታዳልኩት እኔ.....
ኻንቺኑ ኻምፔ ከንቺሬን ብልከው
ከንቺርኽ ለለቱ ከንቺሬን ባረከው
ማን ያውነው ሚስኪን ከንቺር
ለለት ለሞ ሲከረከር
ልቀቂኝ....
ል..ቀ..ቂ..ኝ
በቃኝ በቃኝ ተቆረጥኩኝ
በፍቅርኽ ወዳቅኩኝ...
እንዳ መላእክት ሰይፍ ኻበልባል ከ ለለት
ሁለቱን ኻጣምሬ
ኻይኗ ተጨፍኖ ጉሶ ሰሬኝ ከንቺሯ
.....ወይ መከሬ.....

07/01/2016 ዓ.ም
የኔሁን እንየው



ተሻገሪ ቃለመጥ

THE TRIO ARTISTS (ሦለስቱ ጠቢባን) የስዕል ጥበብን የተቸሩ ሁለቱ መንትያ እህታማቾች (ጋብሬላና ሜሪ) እና ታላቅ ወንድማቸው (ፌራኦል)::






















Firaol
15-12-2012



የመንገደኛ መጣጥፍ

ኑፋቴ ሀሰን

"እመጣለሁ"

ላወራ ሳስብ ምን ይሉት ሰንሰለት ወደ ልጅነቴ እንደሚጎትተኝ አላውቅም....ምናልባት ዛሬዬ ስለደለደመ? ሞረዴን እዛው ህፃንነቴ ላይ ትቼው የመጣሁ ስለሚመስለኝ... ከጣልኩበት ስርጓጉጥ ለመፈለግ? እንጃ!

ላወራ ሳስብ ምን ይሉት ሰንሰለት ወደ ልጅነቴ እንደሚጎትተኝ አላውቅም.... ምናልባት ዛሬዬ ስለደለደመ? ሞረዴን እዛው ህፃንነቴ ላይ ትቼው የመጣሁ ስለሚመስለኝ... ከጣልኩበት ስርጓጉጥ ለመፈለግ? እንጃ!

| ብቻ ገጠር ካሉት ቦታ ፡መሀል ወደሚሉት ከተማ ተዛውሬ የገባሁበትት የመጀመሪያ የህብረተሰብ ትምህርት ክፍል እንዳማይረሳኝ ላወጋህ እመጣለሁ..... <ጋሼ! ሶስተኛው መስመር ምንድነው የሚለው?> ብዬ ጠየቅኩ.... ከችክቸካው ስላናጠብኩት እየተበሳጨ አንብቦልኝ ጠመኔውንና ሰሌዳውን ማፋጨቱን ቀጠለ። ቆየት ብሎ ዞረ...የከነከነውና የሆነ ነገር ትዝ ያለው ይመስል ነበር...<ጋሼ ነው ያልሽኝ?> ብሎ ሳቁን ለቀቀው...መንጋውሪ ተከትሎት አሸካካ....ያኔ ምን ያክል እንደተሸማቀቅኩ፣ የምገባበት ጉያ እንዳጣሁ....ሁለተኛ <ጋሼ> ይሉትን ላልተፋ ለራሴ ቃል እንደገባሁ ልነግርህ እመጣለሁ።

አይገርምህም? ህብረት አስተማሪ ሁኖ የክብር መጥሪያውን እንደውዳቂ ሲያሸቀነጥረው!

| ቡና ልቀዳ ከተሰየምኩ አይዱሩሱ ካልተትጎለጎለ...መተያየትን ካልከለከለ ደስ እንደማይለኝ..... ሁሉን ትቼ መደረሻው የት እንደሚሆን እያሰብኩ ሰንት የጀበና ቡናዎች እንደመየቱብኝ... ሰንቴ የእናቴ «ቀልብሽ የት እየሄደ ነው?» ንግግር ከሄድኩበት እንደሚያባትተኝ ልነግርህ እመጣለሁ።

| ኸሚስ ማታ የሳምንቴ አድማቂ እንደሆነ.... ሁሌም አልጋሽ ላይ ሽንትሽን ትለቂዋለሽ እየተባልኩ የምከለከለውን የማታ ሻይ የሚፈቀድልኝ ቀን መሆኑ እንቅልፌን ታግዬ ሰለዋት፣ ያሲንና ዚክሩን አስኪጨርሱ መጠበቄ ያቀነጠነጠኝ እንደነበር.... የሻይው መንቆርቆር ሙሉን አስትቶ እንደሚያነቃኝ... በቃ ህይዎት በ ሻይ በመጠጣትና ባለመጠጣት የተዘረጋች ድልድል መንገድ እንደነበረችልኝ... የቡና ቁርሳችንን እየገመስን... ስለተገመሰው መንገዴ አወጋህለሁ።

> የአያት ዘመን እንጂ የገዛ ዘመኔ ገጥሞኝ እንደማያውቅ ያሲንን በጋራ እያነበብን ልነግርህ ስለምሻ እመጣለሁ።

| ያሲን ስል÷ አያቴ ቤታችን ሲታደም...አስከ አሁኗ ቅፅበት ድረስ እንደሱ ያለ ለዛ ያለው የያሲን አቀራር ጆሮዬ ዘልቆ እንደማያውቅ.... ለምን እንደሆን ባይገባኝም <ሰላሙን ቀውለን ሚን ረቢ ረሂም> የምትለውን አንቀፅ አስራ ስድስቴ መደጋገሙን አይቼ ለአቅመ መቅራት ስደርስ እኔም ልምዴ አድርጌው እንደቀጠልኩ .... የአያት ዘመን እንጂ የገዛ ዘመኔ ገጥሞኝ እንደማያውቅ ያሲንን በጋራ እያነበብን ልነግርህ ስለምሻ እመጣለሁ።

| የሆነ አመት ላይ ነው ፡ ለልቤ ከቀረቡትም፣ ከልቤ ከራሱም እጅግ ተነጣጥዬ በከረምኩበት ምን እንደቆሰቆሰኝ እንጂ በአንደኛው ጁመዓ የልጅነት ጭቃዬ ወደተቦካበት መስጂድ አቀናሁ - ከልብሽ ተዋሃጂ ሊል ይመስላል።

ትዝታ በቅንጣት የአባራ ብናኝ በኩል ወደሩሕ እንደሚዘልቅ... ናፍቆት በተቆራረጡ ፣ በጀጂ ፣ እምክ እምክ በሚሉ የመስጂድ ምንጣፎች በኩል እያንጎራጎረ ከነፍስ እንደሚጣበቅ... በተፋፋቀ የሳርና የጭቃ ግድግዳ በኩል ከትናንት እንደሚያላትም ... ደግሞ ሰላቱን ለመጀመር ሰልፋችንን አስተካክለን በቆምንበት አሰጋጁ «አላሑ አክበር!» ሲሉ... ያ ድምፅ ከነበርኩበት ጉድባ መንጭቆ በትናንት ሰማዬ ላይ በሞን ያክል ጎይል እንዳንሳፈፈኝ... አሊፍን ያስቆጠረ ጣታቸው፣ በረብሻዬ ተረብሻው የሰደዱት ቁንጥጫቸው ፣ በቅልጥፍናዬ ተደሳስተው ከመዳፌ ያስቀመጡት ናና ከረሜላቸው ፣ ሙሉም ሰልፋን አሳምሮ በዓይነ ሕሊናዬ ሲርመሰመስ ሰላቱን ሳላውቀው እንደተገባደደ ... መስሎኝ በሌላ ሌላው ስባዝን ሰነበትኩ እንጂ የናፍቆት አሊፌ እራሳቸው ኡስታዜ እንደነበሩ... ወደ ጁመዓ እያዘገመን ብተርክልህ እጅጉን እመኛለሁና አረጋጊ ሽርጥህን አገልድመህ ብትጠብቀኝ እወዳለሁ።

|ከዛው የጁመዓ ሰላቴ ማገባደድ ኋላ በሩ ጋር ሰላገኘኋቸው ፡ በደበዘዘ ምስል ዐቅሌ ላይ ስለታተሙ የሚሚያሳሱ እንቡጥ ሴቶች... ሳስታውስ እንደበታቸውን ከፌደል ልሰፋ የተጋሁባቸው... መጫሚያዬን ላስር በተጎነበስኩበት ጆሮዬ የጠለቀ ወጋቸው ከማስደንገጥ ይልቅ እጅጉን ለመገረም እንደጣለኝ... መች እዚህ ደርሰው ስለሙሽርነት እንደሚያወሩ... መች በቅተው ስለሚዜነት ... ስለመተጫጨት ባለእውቀት እንደሆኑ ግራ እንደገባኝ... ጊዜ ይሉት ተገትሮ የቀረው እኔው ጋር ብቻ እንደሆነ ... ሙሉም በዋሽንቱ በኩል ረቂቅ ዜማውን እያፈሰሰ እየጣፈጠ ፡ የኔው ከደረቴ ተሰንጎ እንዳፈነች ማወቄ ትንሽ ትንሽ ልቤን እንደጎሸመች ላቀነቅንልህ እመጣለሁ።



ቅዳሜን ከሳንኮፋ ጋራ

Survive or serve?/ alturism or selfishness ?
መጋቢት 17/2014 ዓ.ም

መነሻ ሃሳብ: ማማ በሰማይ የጸሀፊዋ የመጨረሻ ሃሳብ ላይ ፣ ከማገልገላችን በፊት ለራሳችን መኖር ነበረብን ያለችውን ከዛም ተነስቶ ያለውላይቀር የተባለ የሳንኮፋ አባል የመኖር ቅደም ተከተሎች survive ከዛም serve ነው ባለው ላይ የተደረገ ውይይት

አስበ፡ እኛ ባለፉት ዘመናት serve ባደረጉ ሰዎች ነው የኖርነው፡፡ ጥሩም ሆነ መጥፎ፡፡ አብዛኞቹ ግን እንደተጎዱበት አስባለሁ
ክርስቲያን፡ serve ለማድረግ እኛ መኖር የለብንም? survive passive ማድረግ መሆን ወይስ ራስን መጥቀም?
ፍና ፡ በsurvival ውስጥ ራሳችንን እናውቃለን፣እንጠቅማለንም ብዬ አምናለሁ፣ serve ማድረግ ደግሞ survivalን መቅደም የለበትም።
ልሳን፡ ሰው ራሱን የሚያገኘው serve በማድረግ ውስጥ ነው(survival in service)፡፡ ሁሉም በsurvival ቢኖር አሁን ላይ እኛ አንኖርም ነበር፡፡
ዐማኑኤል፡ serve ለማድረግ አሁን ላይ ያለን እውነት ምን ያህል ተጽዕኖ አለው ?ሁሉም ህይወት ያለው ነገር "will to live" አለው ከevolutionም አንፃር፡
ለምሳሌ፡ Ayn Rand ሰው ራስ ወዳድ መሆን አለበት ይላል፤ በተቃራኒው Che gu vera ለሰው ሀገር ነፃነት የሰራ ለሰዎችም serve በማድረገ የሚያምን ነው እንዴት ታዩታላችሁ?
ሀና፡ serve ስናደርግ የእውነት/ ትክክለኛነቱን እንዴት እንረዳለን ማሚላት ያለብን ነገሮች ምንድን ናቸው? በሀሳብ መብሰል፣ መውሰድ መቻል፣ economy ምን?
ልሳን፡ survival passion መከተል ከሆነ passion ለእኛ serve ማድረግ ቢሆንስ?
ዮርዳኖስ፡ survival ከmorality አንጻር ብናየው ሰው ውጪ እያደረ የቤት ባለቤት መሆን ልክ ነው? serve ለማድረግ ብዙ የምንሰበስብ ከሆነ morally ልክ አይደለም። ለስራችን reward መፈለግ ስናቆም የእውነት selfless እንሆናለን።
ክርስቲያን: ከሁሉም selfless act የመጨረሻው መዳረሻ selfishness ነው። ከselfless act ጀርባ ያለው motive ምንድነው? ራስን/ማህበረሰብን መጥቀም?
አስበ: በስተመጨረሻ ያለው ማግኘት እና ማጣት ተመዝኖ በበለጠው ውጤት የሰው act selfish ወይም selfless ተብሎ ይወሰናል።
ዐማኑኤል: selfness ብለን የምንጠቅሳቸው ሰዎች ማነስ በራሱ ትክክለኛውን/የህይወት ህግ selfishness መሆኑን እያሳየን ቢሆንስ?
ልሳን: ብዙሃኑ selfish ህዝብ በጥቂቶች selfless ሰዎች expense እየኖሩ ቢሆንስ? ስላላየነው የለም ማለት አይደለም።
አብርሃም: survive ማድረግ(ራስን መቻል) በራሱ serve ማድረግ ነው። survival leads to serve
ኪሮስ: selfless ለመሆን ፍቅርና ሞራል ዋና እና አስፈላጊ ናቸው።
ዮርዳኖስ: ለመስጠት መሰጠት አያስፈልግም፣ serve ሁላችንም ውስጥ አለ። እናም ጊዜ አንጠብቅ
ዐማኑኤል: ከmotive በተጨማሪ action ላይ ብናተኩር ።

ቅዳሜን በሳንኮፋ መድረክ
ሀሳብ ከሀሳብ የሚፋጭበት፣ሀሳብ ከሀሳብ የሚፋተግበት፣ሀሳብ ከሀሳብ የሚጋመድበት፣ ቃላት በቀጭን የሚፈተሉበት፣እይታ እንደ ጥጥ የሚባዘትበት፣የዕብለት እርቃን የሚገለጥበት፣ እውነት ጥሩ በፍታ የምትደርብበት ዕለት።
ይምጡ፣ይታደሙ፣ይናገሩ፣ያዳምጡ፣ ይደመሙ።
ዘወትር ቅዳሜ ከምሽቱ 1:30 ጀምሮ ከሳንኮፋ አንባብያን ማኅበር

የቲኺሙ ፎጵ

BIG EYES

ETSEHIWOT





A few years back, I had stumbled upon this gem of a movie which was definitely worth the watch. The movie is about an artist who had silently watched all her works being stolen by a man that she calls her husband for years. None of us need to be an artist to understand what it feels like to not be able to take pride in what we do. And it is worse when the person who is taking the credits is someone who should have supported your dreams and works, which is why it was hard for her to fight back and to tell the truth to the world. This woman's name, if you're already wondering about it, is Margaret D. H. Keane. Perhaps if you go ahead and look her name up you will actually find photos of her and her art works. Indeed, 'Big eyes' is a bio-pic (biographical motion picture) which was directed by Tim Burton and was released in December, 2014 G.C.

The movie actually starts with a newly divorced woman (starring Amy Adams) packing up suitcases for her daughter and herself. Unlike other people though, we see Margaret also packing some of the paintings from the walls of her home; specifically the ones with children who seem to have disproportionally big eyes. As the movie progresses, we find out that Margaret is an artist with a signature style to her art: the big eyes. She then meets Walter Keane (starring Christopher Waltz) at a fair where they were both selling their paintings. He was selling his paintings of the streets of Paris and they eventually start to talk and like each other. They later get married when he offers her an economically safe space for her so that she could keep raising her kid and not lose custody to her former husband.



Walter's manipulative ability working through his easy going, extroverted and amicable traits had made him an excellent sales and Margaret was quite the opposite. So he saw an opportunity to claim her paintings as his when his paintings couldn't sell and he didn't hesitate to take it. It takes Margaret years before she finally decides that she is done with all of it and moves away.

'Big eyes' is not just a mere bio-pic showcasing the life of Margaret Keane. It also brings the concepts of high art vs low art and good art vs bad art in to notice. The signature style of an artist was definitely one of the concepts I have captured while watching the movie (it is also how the writing of this review came about). Furthermore, it exhibits the financial and economical aspects of selling art works and the obstacles and hardships artists would presumably face. In addition, it gives as a peek of what women's right movement was like in the 1950s.

'Big eyes' has been nominated 18 times in different awards and has won three of them. Among the nominations was the Golden Globe Awards nomination for best original song for the song 'Big eyes' by Lana Del Rey.

All in all, this movie is a captivating one and I hope if you get to watch it someday, you will love it too. Let us know what you think of it if you do.

Further suggestions include;

- Big eyes: the screenplay (A book by Scott Alexander and Larry Karaszewski)
- Citizen Keane: The Big Lies Behind the Big Eyes (A book by Adam Parfrey and Cletus Nelson)

ነገረ ጎንደር



“እረ በአያሌው”

በደቡብ ጎንደር ታች ጋይንት ኤፍራታ ምድር ዕትብታቸው በቀበርሞ ፡ የነገሱበት ምድር ሀገር የሆነላቸው፤የስሜን ጎንደር ደጀን ፤ያልተዘመራላቸው እንዳይባሉ ድፍን ጎንደሬ ለሰርግ፣ለጨዋታ፣ለዘፈን ማድመቂያ ስማቸውን የሚያወሳቸው፤ሀቃቸው የተቀበረ፣ታማኝ የሀገር ባለአደራ ፣ስማቸው እንጂ ሰራቸው ያልታወቀላቸው አመድ አፋሽ፣ እምነታቸው ሞኝ ያስባላቸው የዳባቴ መመኪያ ደጃች አያሌው ብሩ ናቸው።

ደጃች አያሌው ከእቴጌ ጣይቱ እህት ልጅ ወይዘሮ ገሠች ብጡል እና አቶ ብሩ ገ/ማርያም ታች ጋይንት ልዩ ስሙ ኤፍራታ የሚባል ቦታ የተወለዱ ሲሆን ዘጎራ ላይ ደ/ር አለማየሁ ዋሌ እንዳሉት የሰው ሀገሩ የተወለደበት ብቻ እንዳልሆነ ማሳያ የሆኑ ናቸው ምክንያቱ ደግሞ እንደ ገዢ የተሾሙበት ስሜን ጎንደር ከተወለዱበት ደቡብ ጎንደር ይልቅ የኔ ስለሚላቸው። ተጓዠ ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩምም ጎንደርን ፍለጋ በሚለው መጽሐፉ የስሜን ገበሬ ያለው ብሎ ያሰፈረውም የስሜን ጎንደር በተለይም ለዳባቴ የልብ ሰው መሆናቸውን ነው።

“አይለቀለቅም ብርሌ ባጓት
የአያሌው ብሩ ሀገር እንዴት ነው ዳባት።።”

ከእሞዬ ምኒልክ ጀምሮ ራስ ተብሎ የመጠራት ማዕረግን ቀል የተገባላቸው ደጃች አያሌው ልጅ ናቸው ተብሎ ራስ መሆኑ ቆየት ብሎ እንደሚሰጣቸው ነግረው ደጃዝማችነትን አብርክተው እሞዬ ያልፋሉ ቆይቶ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ሁለት ጊዜ ባሳዩት የጦር ጀግንነት ቀል ቢገባላቸውም ራስ መባልን ሳያገኙ እንዲያውም የነበራቸው የግብር ገዜ የክብር ቦታን ተነጥቀው ወደ ዳባት ይመለሳሉ ይህን ገዜ የሀገሬው ሰው ሁላችን የምናውቀውን አያሌው ሞኝን ገጠመላቸው።

“አያሌው ሞኝ ሰው አማኝ፤ ሰው አማኝ”

ይህን ከንጉሥ ጋር መሻከራቸውን የሰማው፤ ለሁለተኛ ገዜ ኢትዮጵያን ለመጣል የመጣው ጣልያን ከአርሱ ጋር ከሰሩ የራስ ማዕረግን እንደሚሰጣቸው በስጦታዎች ቢያባብላቸውም የተሰጣቸውን ሁሉ በገዜው ለነበሩ አርበኞች በመሰጠት፤ለመልሱም ጣልያንን ለመዋጋት ጦራቸውን አንስተው የተንቀሳቀሱ ቢሆንም ባንዳ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ከመታማት ግን አልተረፉም በዛም ምክንያት እኛ በደራሲነት የምናውቃቸው በገዜው አርበኛ የነበሩት ሀዲስ አለማየሁ መልዕክት እንዲያደርሱ በተላኩ ሰዓት ደጃች አያሌው በሀሜቱ መቆጣታቸውን እንዲህ ጽፈውት ነበር...

“ለመሆኑ የምኒልክ አልጋ፣የጣይቱ አልጋ፣የጎይለሥላሴ አልጋ የኔ አልጋ ሳይሆን ቀርቶ ነው እኔ አያሌው በገዛ አልጋዬ ደባ ይሰራል ተብዬ የምጠረጠረው ግድየለም፤እንዲያ ያለውን ወሬ ያሰወሩብኝ ጠላቶች ጋር ልብና ኩላሊት መርሞሮ የሚያውቀው አምላክ ያፈራርደኛል።”

ደጃች አያሌው ያልተነገረላቸው አያሌ እውነቶች እንዳሉ እሙን ነው፤ በአያሌውም እውነታቸው ተሸሽጓል ግን የሚተማመኑበት፤ጦር ሲዘምቱ ታቦቱን ሳይዙ የማይወጡት፤ዳባት ላይ ቤተክርስቲያኑን ያሳነጹለት፤ በስሙ ምለው የማይዋሹበት ቅዱስ ገብርኤል ሀቃቸውን ያውጣላቸው፤ ውለታ የዋሉለት የዳባቴ መሬት እና ህዝብ ይመሰክርላቸው እንላለን።

እኛም የጎንደር አዘማሪ እንዳለ በጎንደር ታሪኮች ውስጥ በአንዱ ከደጃች አያሌው ጋር እንዲህ ሸር አልጎበት።

“አያል በጎንደር ሸር እንበል ብሎኝ ነበር”

<u>ዋቢዎች</u>

1. ጎንደርን ፍለጋ፤ሄኖክ ስዩም (ተጓዠ ጋዜጠኛ)
2. ዘጎራ፤አለማየሁ ዋሌ አሸቴ (ደ/ር)



ከእስክንድር ጋር



መምህሩ በስማርት ቦርዱ ላይ ጎላ ብሎ በሚታየው diagnosis of hematologic malignancy በሚል ርዕስ የማያውቀውንና ያልገባውን እውነት በማያውቀውና ባልገባው የቴክናሎጅ ውጤት ተጠቅሞ እንደየ ሀሳባችን እንድንስል በሀሳቡ ይሆናል ብሎ የሳለውን ለማብራራት ይጣጣራል። ክፍሉ ውስጥ ከመምህሩ ድምፅ በቀር የሚሰማው ነገር ፀጥታው ነው። በፀጥታው ውስጥ የሚፈሰው የመምህሩ ድምፅ ኩልል ብሎ ወደ ጆሮ ይገባል። መንገራገጩ ሳይቀር አይጉደፈደፍም። ትምህርቱን እንደሀሳቤ ስስለው የእውቀት ህዋሳቴን እየኳረኮረ በደስታ ይስቃል። በአንክሮ እየሰማሁ እያለ በል ብሎኝ ወደ እስክንድር ዘወር አልኩ። እስክንድር ከክፍላችን ኩል የምትመስለውን (የእኔ መታሚያ ናት)ልጅ እንደ መምህሩ እየሰረቀ ያያታል። ነገር ግን ልቤ ከትምህርቱ ጋር ኑሮ ብዙም ልብ አላልኩትም ነበር። ድንገት ቅፍፍ አለኝና ተመልሼ ዘወር አልኩ እስክንድር ቀና ብሎ አይቷት ይፅፋል።ቀና.....ሾፍ.....አሰብ.....ጎንበስ ይላል። ተከትዬው ቀና ብዬ አየኋት።የጥቁር ቀለምን ውበት ለአለም ለማሳየት ጌታ ከሰማይ የወረወራት ጥቁር እንቁ ትመስላለች። መምህሩን ያለው ገራጫ ነው። ግንባሯ ሲያበራ ጥቁር ብርሀንን ይውጣል የተባለውን ሳይንስ የሻረ ይመስላል። ቅንድቧ የአይኖቿ ሽፍሽፍትና ጭራ ከሩቅ ይጮሀሉ። አይኖቿን ስትገልጣቸው እንደኮከብ ያበራሉ። ከግንባሯ ዝቅ ብሎ ጎድጎድ ብሎ ጀምሮ ቀጥ ብሎ ይወጣና ሰፋ ባሉ ሁለት ቀዳዳዎች የሚጨርሰው አፍንጫዋ የሰውነት ልዩ የገፅ መገለጫ ውበት እንደሆነ ምስክር ነው። በቀይ ቀለም የነደዱ ደንደን ያሉ ከንፈሮቿ አዲስ የምትፈነዳ አደይ አበባ አስመስሏታል።የወተት አረፋ የሚመስሉት ጥርሶቿን ገለጥ ስታደርጋቸው ያስደነብራሉ። ምጥን ያለው አንገቷ ጠረጴዛ ላይ የተደገፉት እጆቿ በቀለም የደመቁት ጥፍሮቿ የወገቧ ቅጥነትና ተቀምጣም ቢሆን ውበቱን ከመግለጥ ያላንቀላፋው መቀመጫዋ...ብቻ ቀሪውን ለማየት ብዙ ነገር ተደራርቦ ጋረደኝ እንጅ እጿጿ...(አቦ እንኳንም ታማሁባት) ናት። ምናልባት እስክንድርም እንደኔ እያያት ይሆን እንዴ ብዬ አየሁት። እሱ እቴ ሁሉን ትቶ በብእሩ አለም ይባትል ይዟል። እርግጥ ነው በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን በማንኛውም ጊዜና ቦታ ቢሆን አይምጣበት እንጂ ከመጣበት ወረቀት ላይ ገንፍሎ ካልወጣለት በቀር እረፍት እንደሌለው ስለማውቅ ምናልባት አሁን የትምህርቱ ርእስ ወይም መምህሩ ከዚች ልጅ ጋር የተገናኙበት አንዳች ምስጢር አግኝቶ ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ። አሁን የዚህ ሰውዬ ክፍለ ጊዜ ባለቀና ባየሁት እያልኩኝ ሳስብ ፓወር ፖይንቱ thank You የሚል እስላይድ ላይ ደረሰና ማለቁን አበሰረኝ። መምህሩም ማጠቃለያ ሰጥቶ ጓዙን ጠቅሎ ወጣ።

እኔም በትልቁ ተንፍሼ ማስታወሻውን ሳብ አደረኩና ሲቸከችከው የነበረውን ፅሁፍ ማንበብ ቀጠልኩ።

"በአንች ቤት ነፃ ሆነሽ ሞተሻል።ሰው ነፃ ፍጥረት ነው ማለት እንደ እውነት ይኖራል ማለት እንጂ እንደሀሳቡ ይኖራል ማለት እንዳልሆነና እንደሀሳብሽ እንዳልሆንሽ ማን በነገረሽ።አልገባሽም እንጂ ገብቶሽ ቢሆን ኑሮ የትኛውም አካል እንደሀሳቡ ለመኖር ማንንም መጉዳት የሌለበት፣ክፋት የማያውቅ፣ጉድለትን የማያስተናግድ ፣መወሰን በሌለው አኗኗር የሚኖር፣ፍፁምና ምልኡ የሆነ ማንነት ያለው አካል መሆንን እንደሚጠይቅ ትረጂ ነበር።እንዲያ ባይሆንማ ኖሮ ስንቱ ይዞሽ ጠፍቶ ነበር፤ስንቱ አንሶላ ተጋፎሽ ነበር፤ ስንቱስ እንዲሁ ገፍትሮ ሰባብሮሽ ነበር፤ስንቱስ ገሎሽ ስንቱስ አድኖሽ ነበር።ግን የሚሆነው እንዲያ አይደለምና አንቺኮ የቱ ምን እንዳሰበ አታውቂም።በዚህ እንኳ የአካልሽን ነፃነት የመሸከም አቅም ውስንነት አልተረዳሽም።ባይገርምሽ ፍፁም የሆነ ነፃነት በዚህ አካላችን ተሰጥቶን ቢሆን ኖሮ የተለያየ ፍላጎት ሲኖረን የመጨረሻ ውጤቱ መጠፋፋት ከመሆን እንደማያመልጥ አልተረዳሽም። ከገባሽ ነፃነትስ ፍላጎትን በእውነት ልክ ሰፍቶ መገኘት ነው።ከገባሽስ ነፃነት ሀሳብን በነባራዊ አለም ላይ ማሳረፍ ነው።ሰው ባለመሞረጥ እንኳ እራሱን የሚያገኝበት ብዙ እውነት አለው።አንቺ ብትረሽውም አይካድም።ከመሆንም ትንሽም እንኳ አይጎድልም።ለምሳሌ ሰው ፈቅዶ አይታመምም፣ሰው ፈቅዶ አይሞትም፣ ሰው ፈቅዶ ምንም አይሆንም፣ ሌለው ቀርቶ ሰው ፈቅዶ አይወለድም፣ ሌላው ቀርቶ ሰው ፈቅዶ አይደኸይም ሀብታም አይሆንም።በርግጥ ከኛ ውስጥ የሰው የአኗኗር ውጥንቅጥ የሚዳስሰው ስውር መዳፍ የሚመራው ስውር አይን የሚሰማው ስውር ጆሮ የሚያከናውነው ስውር አካል ምን አይነት እንደሆነ ያየና የዳሰሰ አለን?የለም። እርግጥ ነው ሰው የፈለገውን የመናገር መብት፣የፈለገውን ጎዳና የመሞረጥና የመጓዝ ፈቃድ፣የተመኘውን ህይዎት የመምራት ነፃነት ...ወዘተረፈ አለው።ከነዚህ ከእያንዳንዳቸው ጀርባ ግን ወገብ የሚያጎብጥ የሀላፊነት ሸክም የሚጭን ውጤት አላቸው።መሞረጥ ይቻላልና ነፃነት በሚመረጡት ነገሮች የተውሰነ ነው።በርግጥ የሚመረጠው ሰው ከሚመረጡት ነገሮች የተረፈ ሀሳብም አካልም ያለው አይደለም።ስለሆነም ሁሉን የመሆን ነፃ ፍቃድ አለኝ እያልሽ ልትሆኝ የማይገባን ከመሆን ብትታቀቢ ይሻልሽ ነበር።እንቢ ብትይ ግን አንድ ህዋስ ተፈጥሮው ከሚፈቅድለት ሁኔታ ውጭ መራባት በመቻሉ ብቻ እራባለሁ ብሎ ቢያምፅ ከሚፈጥረው እሱንም ሆነ በዙሪያው ያሉትን ሁሉ ወደ አለመኖር የሚመልስ እባጭ ከመሆን አታመልጭም።የራሱ የሆነ አኗኗር ባህል ልማድ ባለው ማህበረሰብ ውስጥ ሳይገባሽና ሳትረጂው ነፃ ነኝ በሚል ሰበብ የምትሆኝው መሆን እራስሽንም ዙርያሽንም መከራ ውስጥ የሚከት እባጭ ነውና ቆርጠሽ መጣል እንዳለብሽ የምትረጂ ሁኝ..."ይላል።

እንዲች አይነቷን ሰውን እንዳልገባው ለማስመሰል የሞትደረግ የሹፈት ፈገግታ አውቃታለሁና"እንደውም እኔ ነኝ እብዱ ከአንተ ጥሩ መጠበቄ።"ብዬው ትቼው ወጣሁ።

"ግን የፃፈው ጥሩ ነገር ይሆን እንዴ? እኔ እንጂ..... ሊሆን ይችላል"





የግጥም ደመራ

"ሰው እንቢ ያለለት
የፈጣሪን ስራ
ብቻ መሆን ከንቱ መሆኑን
ሊያውራ
እንጨት እንኳ በአቅሙ
በአብሮነት ሊመራ
ችቦ ተሰብስቦ ይሰራል
ደመራ"

ሳንኮፋ የአንባብያን ማኅበር

እናንብብ፣እንለወጥ፣እናካፍል

የግጥም ችቧችን

የግጥም ደመራ: በመስቀል ደመራ ዕለት "ችቦ ተሰብስቦ ይሰራል ደመራ" በሚል መነሻ ስንኝ ተነስቶ ስንኝ እየተቀጠለና እየተጨመረ የሰራነው ግጥም ነው። ለተሳተፋችሁት ሁሉ ምስጋናችን ይድረሳችሁ

ችቦ ተሰብስቦ ይሰራል ደመራ
እጠብቅሻለሁ መስቀል አደባባይ
እንዳትቀሪ አደራ
ያልመጣሽ እንደሆን የጠበቀሽ አይኔ
አልቅሶ አያባራ
እንዲው ያማትራል አንዴ እዚ እንዴ እዛ
ተይ ችላ አትበይው ልቤን እንደዋዛ
.....
መቅረት መቅኔው ይፍሰስ ይኮስምን አካሉ
ነይልት ለልቤ አንቺው ነሽ መስቀሉ
የደመራው ብርሀን ለሁሉ ሲያበራ
እንዴት የኔ ፀሀይ ታዘቅዝቅ ጀምበሯ
.....እንዳትቀሪ አደራ.....
ሰሞትልሽ አትቅሪ
በቅድስት ዕሌኒ
ይሄውልሽ መስቀሌ አንቺ ከቀረሽማ
ችቦ አካሌ ይጤሳል
የተደበቅሽበትን ስለማውቀው
ጢሱ አካሌ ላንቺ ይሰግዳል
ልቤ እኮ ሞኝ ነው ፈጣሪን ይክዳል
.....ሰሞትልሽ አትቅሪ.....
.....አይገርምሽም.....
ካህናት ደመራውን እየዞሩ አጠኑት
አንቺ ሳትመጪ እስኪ እንዴት ያቃጥሉት
እንዴት ይለኩሱት ገብተው ከመሐሉ
አንቺ የሌለሽበት አይደምቅም በዓሉ
.....አይገርምሽም.....
ተማሪው በሞላ መስቀል መስቀል አለ
አንቺን ካወቁማ ቢጠሩሽ ምናለ
ምናለ ቢያወጡሽ ተራራውን ምሰው
ቦታሽን ቢያገኙት እጣኑን አጢሰው
ምን ጎሎ በመስኩ ምን ጎሎ በሜዳው
አንቺ ቀረሽ እንጂ ይሄው ሽንኮራ አገዳው
.....ለነገሩ አይጥምም.....
አንቺ የሌለሽበት ምኑ ይጥማል
ይራዘም በአሉ
ይበተን አዳሜ ይታወጅ ለሁሉ

ሊጠሩሽ ነው መሰል ጭራሮ አያለሁ
ችቦ እንሰራም የሚል ድምፅን እሰማለሁ
ዳሩ ግን
ጠላት ምቀኞችሽ ቆሻሻውን ጣሉ
የተንኮል ጥላቻን ደመናን አጠሉ
ፈጣሪ ቢፈቅድ እሌኒን ያስነሳ
ያከተመ ሚመስል ነብስሽ እንዲነሳ
ከልጅ ወደ ልጅልጅ ስምሽ እንዲወሳ
ሀገሬ ወደአምላክ እጆችሽ ይነሳ።

የጭራሮ ህብረት ይሰራል ደመራ
እጠብቅሻለሁ አንቺዬ አደራ
ሰልክሽም የለኝም ጅንጀና አላውቅ ከቶ
መስቀል ብቅ ብዬ ልንካሽ በእስክሪፕቶ
ከኔ የሚዋጣ ችቦ ነው ብዕሬ
ደመራ ምሰራው እንዲ ነው አብሬ
ከልቤ ሰርጣሰርጥ ከልቤ ቋጠሮ
ፀሎትና ግጥም ይሄዳል ገብሮ

በሞሐመድ ልደት መስቀልም ከዋለ
ልዩነት ባንድነት እንዲ ተፈተለ
ይጫር እስኪብርቶ ከንግዲም ተስፋ አለ ።
.....
.....


የመስቀል ወፍና የኣዳይ ኣበባ፣
ቀጠሮ እንዳላቸው መስከረም ሲጠባ
ማን ያውቃል?
[መንግሥቱ ለማ]

ስለእኛ



ሳንኮፋ ቤተመጻሕፍት ከ2800 በላይ የሚሆኑ የታሪክ፣ ልቦለድ፣ ፍልስፍና እንዲሁም የሥነልቦና መጻሕፍትን የያዘ ቤት ነው። የግጥም መድብሎች፣ ወጎችና ትምህርታዊ መጻሕፍትም እንደልብ ይገኛሉ። መጻሕፍቱ በአማርኛ፣ በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በዓረብኛና በቱርክኛ ቋንቋዎች የተጻፉ ናቸው።

አባል መሆን | መጻሕፍት ማንበብ | መወያየት | መጻሕፍት መለገስ

አባል ለመሆን

10 ብር
እና
ጉርድ ፎቶ ብቻ

ክንውኖች

ንባብ
ውይይት
ዓርብን በሳንኮፋ
የተልያዩ መርሐ
ግብራት

ሃሳብና አስተያየት

+251947485623
+251946570637
@poco_loc0
@kidan_26
@opalg19
t.me/sankofabooks
sankofa Readers
Association

እናንብብ፣ እንለወጥ፣ እናካፍል!

ፍኬሪት

ቀጣይ እትኽ በቅርቡ ይጠብቁ!

እናንብብ፣ እንለወጥ፣ እናካፍል!

ምርትና አገልግሎትዎን እዚህ ያስተዋውቁ!

+251947485623
+251946570637



እናንብብ፣ እንለወጥ፣ እናካፍል!